# የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን

# የሥርዓት መጽሐፍ

The Ethiopian
Kale Heywet Church
Service Book

2012 ዓ.ም
አዲስ አበባ

Scanned by CamScanner

# የሥርዓት መጽሐፍ

# The Ethiopian Kale Heywet Church Service Book

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
በአርባምንጭና አካባቢዋ አጥቢያ
ቤተክርስቲያናት ኅብረት
የዩኒቨርስቲ ፋር አጥቢያ ቤተክርስቲያን

Scanned by CamScanner

ይህ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የሥርዓት መጽሐፍ
ነሐሴ 8 – 11/1988 ዓ.ም ቦኖሻ በተደረገው 31ኛው የመሪዎች
ጠቅላላ ጉባዔ ላይ ጸደቀ።

14-17August1996
Bonesha

# የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን የሥርዓት መጽሐፍ

# The Ethiopian Kale Heywet Church
# SERVICE BOOK

Revised Edition 2020

የመጀመሪያ እትም፤ 1989 ዓ.ም

**የተሻሻለው እትም 2012 ዓ.ም**

አሳታሚና አከፋፋይ
የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
የኮሙኒኬሽንና የሥነ ጽሑፍ መምሪያ

ፖ.ሳ.ቁ 5829 ስልክ 011-5-50-59-08/011-5-50-59-11

አዲስ አበባ



Scanned by CamScanner

# ማውጫ


ሀ. መልእክት ........................................................IV

ለ. መግቢያ ........................................................V

ሐ. ስለ መጽሐፉ አጠቃቀም ........................................VII


## ክፍል አንድ


1. የእሁድ አምልኮ ሥርዓት .......................................... 1
2. የጥምቀት ሥርዓት.................................................. 5
3. የጌታ እራት መታሰቢያ ሥርዓት .................................. 8
4. የጋብቻ ሥርዓት ................................................... 11
5. ሕጻናትን ለእግዚአብሔር የማስረከብ ሥርዓት ...................... 17
6. የቀብር ሥርዓት.................................................... 19
7. የሽማግሌዎች ሹመት ሥርዓት....................................... 21
8. የዲያቆናት ሹመት ሥርዓት .......................................... 24
9. የወንጌል መልዕክተኞች፣ የመጋብያን እና የአስተማሪዎች ሹመት ሥርዓት ....... 26
10. የከፍተኛ ሥነ መለኮት ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ምረቃ ሥርዓት.............. 30
11. የመሰረት ድንጋይ የማኖር ሥርዓት ................................ 34
12. የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ምረቃ ሥነ ሥርዓት .......................... 35
13. ልዩ ልዩ ማሳሰቢያዎች ............................................ 37
14. የገቢ አሰባሰብ.................................................... 37
15. የመዘምራን የደንብ ልብሶች ዓይነትና ቀለማት ....................... 37
15. የቤተ ክርስቲያኒቱን ዓርማ በተመለከተ ............................. 41


## ክፍል ሁለት


መ. የምስክር ወረቀቶች ..........................................43 – 46




Scanned by CamScanner

# የዋና ጸሐፊው መልእክት

የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ባለፉት ዘጠኝ ዓሥርት ዓመታት ውስጥ ሁሉን ቻይ በሆነው በእግዚአብሔር ጸጋና እርዳታ ለአገራችን ሕዝብ የወንጌሉን የምሥራች በማዳረስ፣ በየስፍራው ቤተ ክርስቲያናትን በመትከል የእርሱን መንግሥት እንዲሰፋ የበኩሏን ጥረት ስታደርግ ቀይታለች። ከአገራችን አልፎ ለሌሎች አገሮች ሕዝቦችም ጭምር የክርስቶስን ወንጌል ለማድረስ ሚስዮናውያንን መላክ ጀምራለች። ለዚህ ሁሉ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን።

ቤተ ክርስቲያኒቱ ባሳለፈችው ዓመታት ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ በመመስረት የቤተ ክርስቲያን አገልግሎትን ሥርዓት ባለው መንገድ እየተመራች እዚህ ደርሳለች። ባለፉት ዓመታት ያገለገሉ የቤተ ክርስቲያናችን አባቶች ጌታን በመውደድ እግዚአብሔር የሰጣቸውን የመሪነት አደራ ጠብቀው በዚህ ዘመን ላለነው ኃላፊነቱን አስተላልፈዋል። ዛሬም በሕይወት ያሉት ከአጠገባችን ሳይለዩ በጸሎታቸው እየደገፉን፣ ያለፉባቸውን የታሪክ ጉዞ ዱካ መለስ ብለው እያመለከቱንና በእኛም ዕቅድ ውስጥ እየተሳተፉ ከዕድሜና ከእውቀት ባገኟቸው ዘርፈ ብዙ ልምዶች እያካፈሉን ይገኛሉ።

ሐዋርያው ጳውሎስ፤ “ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን” (1ቆሮ. 14:40) በማለት በእግዚአብሔር ቤት የምናከናውናቸውን ነገሮች በአግባብና በሥርዓት ማድረግ እንዳለብን ፅኑ ምክር ሰጥቶናል። በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ቃሉን ዋና መመሪያዋ በማድረግ ለምትሰጣቸው አገልግሎቶች እንዲሁም በቤተ ክርስቲያን ለሚፈጸሙ ሥርዓቶች ሁሉ ወጥ የሆነ መመሪያ በማዘጋጀት የምትሰጣቸው አገልግሎቶች በአግባብና በሥርዓት እንዲካሄዱ ይህ ቀደም ብሎ የተዘጋጀውን የሥርዓት መጽሐፍ ከዘመኑ ጋር በተገናዘበ መንገድ አንዳንድ ማሻሻያዎችን በማድረግ ለቤተ ክርስቲያን መመሪያ ይሆን ዘንድ አቅርባለች። በየመዋቅሩ ያሉ የቤተ ክርስቲያናችን መሪ አገልጋዮችም እነዚህን ሥርዓቶች በትክክል ተግባራዊ የማድረግ እና የማስደረግ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አደራ ለማለት እንወዳለን።

**“ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።” ሮሜ. 11:36**



Scanned by CamScanner

# መግቢያ

ቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ ደም ተዋጅታ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ከልዑል አምላክ ጋር በጸጋው ዕርቅ ያገኘች፣ ቅድስትና ንጽሕት የሆነች የክርስቶስ አካል ነች።

ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ዘለዓለማዊ ዕቅድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሳዔ የተቀደሰች፤ የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንና የቅዱሳን ኅብረት እንደሆነች በ1ቆሮ. 1፡2 ላይ እንደሚከተለው ተገልጾአል፤ "ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት የእነርሱና የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው፣ ከሚጠሩት የእኛ ጌታ የሆነውን የኢየሱስ ክርስቶስን ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን ለተጠሩት…"

ቤተ ክርስቲያንንን በደሙ የመሰረተ፣ ራስና መደምደሚያዋም የሆነ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። (ኤፌ. 5፡23፣ ቆላ. 1፡18)። ሕያው ቤተ ክርስቲያን ስለሚኖራት ታላቅ ኃይልና አሸናፊነትን በተመለከተም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለጴጥሮሱ- "…ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፤ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም፤" (ማቴ. 16፡18) በማለት አረጋግጦልናል። በሐዋ. ሥራ 20፡28 ላይም፤ "በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን…" የሚል መሰረታዊ ሃሳብ ተጠቅሷል።

ሐዋርያው ጳውሎስም በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ያውቅ ዘንድ ለጢሞቴዎስ የሚከተለውን ሃሳብ ጽፎለታል፤ "ቤቱም የእውነት ዓምድና መሰረት፣ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው፤" (1ጢሞ. 3፡15)።

"ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ፣ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ፤" (ማር. 16፡15) የሚለውን የታላቁን ተልእኮ መለኮታዊ ትዕዛዝ በምድር እንድታስፈጽም ሕያው አደራ የተቀበለችው ቤተ ክርስቲያን ነች። ቤተ ክርስቲያን በቅዱስ ቃሉ መሰረት አድጋና ሰፍታ ለብዙዎች ማረፊያና መጠለያ እንድትሆን፣ በክርስቶስ ደም የተመሰረተው



Scanned by CamScanner

የቅዱሳን አንድነትና ኅብረት እንዲጠናከር የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምዕመኑ በእግዚአብሔር ቃል መሰረት "ሁሉ በአግባብና በሥርዓት" (1ቆሮ. 14፡40) እንዲከናወን ኃላፊነትና አደራ ተሰጥቶአቸዋል።

የቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ዋና ሥርዓቶች ይህን በመሰለ ሁኔታ ተዘጋጅተው በአንድ ጥራዝ እንዲታተሙ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያትም ቤተ ክርስቲያናችን ዛሬ ከደረሰችበት ግዙፍ ተቋማዊ አደረጃጀት እና የአጥቢያዎች ቁጥር ብዛት አንጻር የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች፣ አገልጋዮችና ምዕመናን አንድ ወጥ በሆነ መልክ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓቶች እንዲያስፈጽሙ ለማስቻል ታስቦ ነው።

ይህ የሥርዓት መጽሐፍ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋም እና በሥራ ላይ ያለ የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት አድርጎ እና ከተገለጹት ሰነዶች ላይ የተገለጹ አቋሞችን እና ደንቦችን አክብሮ ተፈጻሚ እንዲሆን የተዘጋጀ ነው። መጽሐፉ ከላይ እንደተገለጸው ቦናሻ በተደረገው 31ኛው የመሪዎች ጠቅላላ ጉባዔ ላይ የጸደቀ ቢሆንም በ2007 ዓ.ም በሲዳማ አርቤጎና በተደረገው የቤተ ክርስቲያኒቱ ጠቅላላ ጉባዔ እንዲሻሻል በተወሰነው እና ለብሔራዊ ቦርዱ በተሰጠው ውክልና መሰረት በ2012 ዓ.ም በተደረገው የቦርድ ስብሰባ ላይ ጸድቆ ሥራ ላይ ውሏል። በአግባቡ ጥቅም ላይ ውሎ ለእግዚአብሔር አምላካችን ክብር፣ ለቤተ ክርስቲያንና ለምዕመኑም ጥቅም እንዲሆን ጸሎታችን ነው።



Scanned by CamScanner

# ስለ መጽሐፉ አጠቃቀም

ይህ የሥርዓት መጽሐፍ ለመላው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት በሙሉ እንዲያገለግል ታቅዶ በጥንቃቄ የተዘጋጀ መጽሐፍ ነው።

መጽሐፉ እንዲዘጋጅ ያስፈለገበት ዋና ዋና ምክንያቶች፤

ሀ. በእያንዳንዱ የቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚፈጸሙት መሰረታዊ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች ወጥ በሆነ አንድ ዓይነት አሰራር እንዲካሄዱ፤

ለ. የቤተ ክርስቲያን ቀደምት አባቶች ቤተ ክርስቲያንን ይመሩና ያስተዳድሩ የነበረው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረትነት ባላቸው ሥርዓቶችና አግባብ እንደነበረና ቀጥሩ ከዕለት ወደ ዕለት እየበዛ የሚሄደው መጪው ትውልድም በዚሁ አባቶች በተዉልን ፈለግ እንዲራመድ ለማስቻል፤

ሐ. በመላው የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ዙሪያ የሚያገለግሉ ዘማርያን የማዕረግና የጌጥ ልብሶች የስፌት ሞድ ወጥ የሚሆንበትን ሥርዓት ለማመልከትና ዝርዝር ሁኔታውንና አፈጻጸሙን ለማሳወቅ።

መ. የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና ምዕመናን በሙሉ የቦታ ርቀትና ቅርበት ሳይወስናቸው ተመሳሳይ ሥርዓቶችን በሁሉም አካባቢ በመፈጸምና የቤተ ክርስቲያኒቱ ክብርና በመንፈስ ቅዱስ አንድነት የጸናው ኅብረት ተጠብቆ እንዲቀይ ለማስቻል ይህ መጽሐፍ ሊዘጋጅ ችሏል።

በመጽሐፉ ውስጥ ትኩረት የተሰጠው እያንዳንዱ ሥርዓት ቅደም ተከተሉን ጠብቆ እንዲካሄድ የሰዓት አጠቃቀሙን ለመወሰንና አላስፈላጊ የሆኑ መፋለሶች እንዳይኖሩ ለመርዳት እንዲያመችና ገባዔውን አንዳንድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆኑ ልምምዶች ለመከላከል ታስቦ እንጂ በእያንዳንዱ ሥርዓት ላይ የሚነበበው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፣ የሚጸለየው የጸሎት ዓይነትና የሚነገሩት ንግግሮች ሁሉ በዝርዝር በዚህ መጽሐፍ ውስጥ አልተገለጹም።



Scanned by CamScanner

## 1. የእሁድ አምልኮ ሥርዓት

### 1.1 የአምልኮ ትርጉም፡-

አምልኮ ለእግዚአብሔር ብቻ በመንፈስ፣ በእውነት በፍቅርና በመታዘዝ የሚቀርብ ስግደት፣ ውዳሴ፣ ንስኃ፣ ጸሎት፣ ምልጃና ጸሎት ነው:: ዘጸ. 23፡25፣ ዮሐ. 4፡23 — 24፤ ዕብ. 12፡28:: አምልኮ በመዘመር፣ ቃሉን በመስማት፣ ካለን በመስጠትና ለሌሎች በማካፈል፣ መላው እኛነታችንን ለእግዚአብሔር አሳልፎ በመስጠት (ሮሜ. 12፡1) ...ወዘተ የሚገለጥ ነው:: በሕያው እግዚአብሔር ፊት ራሳችንን አዋርደን ስናመልከው፣ እውነተኛ ንሥኃም ስንገባ የኃጢአት ይቅርታንና ምህረትን እናገኛለን፤ እንደ ፈቃዱም የለመንነውን እንቀበላለን::

በዋነኛነት በቤተ ክርስቲያናችን የጋራ የአምልኮ ሥርዓታችንን የምንፈጽምበት ቀን እሁድ ነው:: እሁድ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሞትን ድል አድርጎ የተነሳበት ዕለት ስለሆነ፣ መንፈስ ቅዱስ የወረደውና ቤተ ክርስቲያንም በሐዋርያት ስብከት የተመሰረተችው በዚሁ ዕለት ስለሆነ አምልኮአችንንና ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ሥርዓቶችን የምንፈጽመው የጌታ ራትን መታሰቢያ የምንወስደው በእሁድ ዕለት መሆን ይገባዋል::

### 1.2 የዕሁድ አምልኮ ሥርዓት

1.2.1 አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ከአቅም በላይ ችግር ገጥሞት ካልሆነ በስተቀር ከቤተ ክርስቲያን የጋራ የእሁድ አምልኮ መቅረት የለበትም::

1.2.2 የአምልኮ ማካሄጃ ሰዓትም መከበር ይኖርበታል:: የሚጀመርበትም ሆነ የሚያልቅበት ሰዓት መጠበቅ አለበት::

1.2.3 የአምልኮ ሰዓት ሳይጠናቀቅ መሄድ፣ በጸሎት ሰዓት በአዳራሹ ውስጥ በመረማመድ፣ የቃለ መልእክት እና ሌሎች መርኃ ግብሮች እየተካሄዱ እያለ የጉባዔውን ሃሳብ በሚበትን መልኩ



Scanned by CamScanner

ያለ አግባብ መንቀሳቀስ ተገቢ አይደለም።

## 1.3 የዕሁድ አምልኮ ቅድመ ዝግጅት:-

1.3.1 ወንጌላውያን፣ ዲያቆናት፣ መጋቢያንና አገልጋይ መሪዎች፣ የልጆች፣ የወጣቶችና የሴቶች አገልግሎት መሪዎች፣ ሁሉ ቀድመው በመገኘት ለአምልኮ መርኃ ግብሩ ሁኔታዎችን በማመቻቸትና በጸሎት መቆየት ይኖርባቸዋል።

1.3.2 የዕለቱ ፕሮግራም መሪ፣ መዘምራን፣ መልእክት አቅራቢውና ለዕለቱ የተመደቡ አስተናጋጆች ፕሮግራሙ ከመጀመሩ በፊት በጋራ ለአጭር ጊዜ ጸልየው ወደ አምልኮ አዳራሽ ይገባሉ።

1.3.3 የዕለቱ አገልጋዮች የአለባበስ ሥርዓት አግባብ ያለው፣ አውዱን የጠበቀ፣ እግዚአብሔርን የሚያስከብርና የሰዎችን የአምልኮ ትኩረት የማያውክ መሆን ይኖርበታል። በቤተ ክርስቲያኒቱ ለአገልግሎት አስፈጻሚዎች (ለዲያቆናት እና ለልዩ ልዩ ሥርዓት አስፈጻሚዎች) የተዘጋጀ ልብስ ቸል ሳይባል ወጥነት ባለው ሁኔታ መዘጋጀትና መለበስ አለበት።

## 1.4 የአምልኮ መርኃ ግብር ቅደም ተከተል

መደበኛ የአምልኮ ፕሮግራሞች እነዚህን ማካተት ሲኖርባቸው ልዩ የአምልኮ ፕሮግራሞች ግን ከነዚህ ተጨማሪ መርኃ ግብሮችን ሊያካትቱ ይችላሉ።

1.4.1 ጉባዔው መደበኛ ፕሮግራም እስኪጀመር ድረስ በጸሎት እንዲቆይ ይደረጋል። የጉባኤ የጸሎት መሪ የጸሎት ርዕሶችን በመስጠት ጉባኤው በየግል እንዲጸልይ ማድረግ ወይም የሚጸልዩ ሰዎችን በመጋበዝ ወይም እራሱ (እራሷ) መጸለይ ይችላል/ትችላለች። የጸሎት ርእስ ከሰጡ በኋላ ግን የሚጸልዩ ሰዎች ሃሳባቸውን ሰብስበው በተሰጠው ርእስ ላይ ለመጸለይ እንዳይቸገሩ ብዙ ንግግር ማብዛት አስፈላጊ አይደለም።



Scanned by CamScanner

1.4.2 ፕሮግራም መሪው/ዋ ወይም በእርሱ/በእርሷ ግብዣ የሚነሱ የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ፣ የሽማግሌዎች ስብሳቢ፣ ወይም ሌሎች መሪ አገልጋዮች ጉባዔውን እንኳን ደህና መጣችሁ ካሉ በኋላ ፕሮግራሙን በጸሎት ይከፍታሉ።

1.4.3 የዕለቱ ፕሮግራም መሪ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሕዝቡን ለአምልኮ የሚያዘጋጅ አንድ ክፍል ካነበበ በኋላ የአምልኮ መዝሙር መሪዎችን ይጋብዛል። በመክፈቻ ላይ ረጅም ንግግር ወይም ስብከት ማካሄድ አይገባም።

1.4.4 የአምልኮ መዝሙር መሪዎች/የጉባዔ መዝሙር መሪዎች/ ጉባዔውን ሊያሳትፍ በሚችል ሁኔታ ዝማሬውን ይመራሉ። የአምልኮ መዝሙር መሪዎችም ዋናው ተግባራቸው ሕዝቡን በዝማሬ አምልኮ መምራት ስለሆነ ረጅም የመግቢያ ስብከት አዘል ንግግሮችን ሊያበዙ አይገባም። ከዝማሬ በኋላ ላሉ መርኃ ግብሮች ሰዓት ላለመሻማት የተመደበላቸውን ሰዓት ጠብቀው ሊያቆሙም ይገባል።

1.4.5 መዘምራን /ሶሎ ዘማሪ/ ለዕለቱ ያዘጋጁትን ከ2 - 3 መዝሙሮችን ያቀርባሉ።

1.4.6 ከዕለቱ ዲያቆናት ወይም የጉባዔ አስተናጋጆች አንዱ እንዲጸልይ ከተደረገ በኋላ ሕዝቡ በጸጥታ የመባ ስጦታ ያቀርባል።

1.4.7 የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ወይም ሽማግሌ ጉባዔውን ሰላም በማለት አዳዲስ እንግዶች ካሉም አቀባበል ካደረገ በኋላ የዕለቱን የቤተ ክርስቲያን ማስታወቂዎችን ይናገራል።



Scanned by CamScanner

1.4.8 ለልጆች የተዘጋጀ ትምህርት ካለ ለልጆች ከተጸለየ በኋላ እነርሱ ወደተዘጋጀላቸው መማሪያ ክፍሎች ይሄዳሉ።

1.4.9 የዕለቱ መልእክት አቅራቢ ከቃለ እግዚአብሔር መልእክት ያቀርባል። መልእክት አቅራቢው ወይም የአጥቢያዩቱ መጋቢ ወይም ወንጌላዊ አዳዲስ ወደ ጌታ የሚመጡትንና በንስኃ የሚመለሱ ሰዎችን ይጋብዛሉ።

1.4.9 የቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ፣ ሽማግሌ ወይም የሽማግሌ ተወካይ ጉባዔውን በሐዋርያት ጸሎት ከመራ በኋላ በቡራኬ የዕለቱን ፕሮግራም ያጠቃልላል። ዘኁ. 6:24 — 26፣ መዝ. 20:1 - 5፣ 2ኛ ቆሮ. 13:14 ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ክፍሎችን ለቡራኬ ማንበብ ይቻላል።

1.4.10 ምዕመኑ ፕሮግራሙን አጠናቅቆ ከጸሎት ቤት ሲወጣ መጋቢው ወይም የመሪዎች ተወካይ ለሕዝቡ ሰላምታ በመስጠት ያሰናብታሉ።

ማሳሰቢያ፡-

ሀ/ የአምልኮ ፕሮግራም ዝርዝር ለየዕሁዱ በየአጥቢያው የጊዜ ሰሌዳ መዘጋጀት አለበት። የቤተ ክርስቲያኒቱ አገልጋይ መሪዎች በወጣው የአምልኮ ሰሌዳ መሰረት መካሄዱን ይከታተላሉ።

ለ/ የአምልኮ ፕሮግራሙ በተቻለ መጠን ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ከ2:00 — 2:30 ባለው ጊዜ መጠናቀቅ ይኖርበታል።

ሐ/ በአምልኮ ወቅት ሁሉ በሥርዓትና በአግባብ መሆን ስለሚኖርበት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆኑ ልምምዶችና ልቅ ከሆኑ እንቅስቃሴዎች በተለይ በመድረክ ላይ የሚያገለግሉ አገልጋዮች እንዲጠበቁ ማድረግ ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ፡- የጋራ ጸሎት መደማመጥ የሌለበት ሁሉ በየግሉ የሚጮህበት መሆን የለበትም፤ በጉባዔ መካከል የማይተረጎም የልሳን ንግግር መኖር የለበትም (1ኛቆሮንቶስ 14:27-28)፤



Scanned by CamScanner

በዝማሬ ወቅት አዋኪ ተግባራት ሲፈጸሙ መታየት የለባቸውም።

# 2. የጥምቀት ሥርዓት

## 2.1 የጥምቀት ትርጉምና አስፈላጊነት

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የጥምቀትን ሥርዓት የተቀበለችው በማቴዎስ ወንጌል ምዕ. 28፡19 — 20 እንደተጻፈው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ "እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፣ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ" በማለት ያዘዘውን ትዕዛዝ ለመፈጸም ነው።

የአንድ ሰው ደህንነት የተመሰረተው በእምነት ላይ ሲሆን የጥምቀት ሥርዓትም እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፤ "ያመነ የተጠመቀ ይድናል፤ ያላመነ ግን ይፈረድበታል፤" (ማር. 16፡16) በማለት ማረጋገጫ ሰጥቶናል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ የጥምቀትን ሥርዓት የሚፈጽም ሰው ከክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ ጋር መመሳሰሉንና በአዲስ ሕይወት መኖሩን የሚገልጽበት ምሳሌያዊ ድርጊት ስለሆነ የጥምቀት ሥርዓት አስፈላጊ መሆኑን በሮሜ. 6፡3 — 4 እንዲህ ሲል ገልጾታል። "ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደተነሳ እንዲሁ በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።"

የጥምቀትን ሥርዓት የፈጸመ አንድ አማኝ በቤተ ክርስቲያን አባልነትና አገልግሎት የበለጠ የተሳትፎ ድርሻ ስለሚኖረው ይህ ሥርዓት ለአገልግሎትም በር ከፋች እንደሆነ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታምናለች።



Scanned by CamScanner

## 2.2 የጥምቀት ሥርዓት አፈጻጸም

2.2.1 የቤተ ክርስቲያን ምዕመናን ልጆች ዕድሜአቸው 15 እና ከዚያ በላይ ሲሆን የጥምቀት ትምህርትና የእምነት ማጽኛ ትምህርት ከተቀበሉ በኋላ እንዲጠመቁ ይደረጋል።

2.2.2 አዲስ ወደ ጌታ የሚመጡ ሰዎች የደህንነት ትምህርት በጥልቀት ከ4 - 6 ወራት ተምረው እንዲጠመቁ ይደረጋል።

2.2.3 የጥምቀት ሥርዓቱ በጥልቅ ውኃ በማጥለቅ ይፈጸማል።

2.2.4 ጥምቀት ተጠማቂው በሌሎች አማኞች ፊት አዲስ ሕይወት መጀመሩን የሚመሰክርበት ሥርዓት ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን እንደ አመቺነቱ አባላት ቢገኙበት ጉባዔ የጥምቀት ሥርዓቱ ሊፈጸም ይገባል። በጉባዔ ፊት የሚካሄዱ የጥምቀት ሥርዓቶች ወቅት አጥማቂው የቤተ ክርስቲን አገልጋይም ሆነ ተጠማቂዎች አውዱን የሚመጥን አለባበስ ለብሰው ሥርዓቱን ሊያካሂዱ ይገባል።

## 2.3 የጥምቀት ሥርዓት አፈጻጸም ቅደም ተከተል

2.3.1 ተጠማቂዎች፣ አጥማቂዎችና ምዕመናን የተዘጋጀላቸውን ስፍራ ይይዛሉ፤

2.3.2 የሥርዓቱ አስፈጻሚ አገልጋይ ጥምቀትን በተመለከተ ከመጽሐፍ ቅዱስ አጭር መግለጫ ከሰጠ በኋላ፣ (የንባብ ክፍል፤ ለምሳሌ ከሮሜ. 6፡1 - 7፣ ከኤፌ. 4፡4 - 6፤ ቆላ. 2፡ 12 - 13 ተመርጦ ሊነበብ ይችላል)

2.3.3 ተጠማቂዎች ቃል ኪዳን ይገባሉ።

2.3.4 አጥማቂው የተጠማቂዎችን የማረጋገጫ ቃል እየተቀበለ ማለትም በክርስቶስ ሞት፣ ትንሳኤና ዳግም ምጽዓት ማመኑን በማረጋገጥ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ



Scanned by CamScanner

ስም ያጠምቃል።

2.3.5 ለተጠማቂዎች ሰርተፊኬት ወይም የአባልነት መታወቂያ ይሰጣል።

2.3.6 በመጨረሻም ተጠማቂዎች የጌታን እራት መታሰቢያ ወስደው የዕለቱ ሥርዓት በጸሎት ይፈጸማል።

2.3.7 ተጠማቂዎች ስማቸው እና ተገቢውን የጥምቀት መስፈርት አሟልተው መጠመቃቸውን የሚገልጽ የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ማረጋገጫ ያረፈበት በቤተ ክርስቲያኒቱ ዋና ጽ/ቤት የተዘጋጀ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል።

## የተጠማቂዎች ቃል ኪዳን

1. እኔ በዛሬው ዕለት የጥምቀት ሥርዓትን ስፈጽም ስድሳ ስድስቱ የብሉይና የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት የእግዚአብሔር ቃል እንደሆኑ፣ ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ሥልጣን ያለውና ምንም ስህተት የሌለበት መሆኑን ሙሉ በሙሉ አምኜ ተቀብያለሁ።
2. በመንፈስ ቅዱስ አስረጂነትና በሰዎች ምስክርነት ከኃጢአት ንስኃ ገብቼ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኔን ለማዳን በፈጸመው የቤዛነት ሥራ ደህንነትንና የእግዚአብሔር ልጅነትን ሥልጣን እንዳገኘሁ አምናለሁ።
3. የእግዚአብሔር ቃል በሚያዝዘው መሰረት ለኃጢአት ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር መሞቴንና እንዲሁም በአዲስ ሕይወት ከእርሱ ጋር ለመኖር መነሳቴን በሚገልጽ አንዲት ጥምቀት በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም አምኜ መጠመቄን አረጋግጣለሁ።
4. ከመንፈስ ቅዱስ በሚገኝ ፍቅርና ኅብረት ከእግዚአብሔር ልጆች ጋር አንድ አካል ሆኜ ለመኖር ቃል እገባለሁ።
5. ቤተ ክርስቲያን በምትመድበኝ የአገልግሎት ድርሻ በፍቅርና በመታዘዝ ለማገልገልና በግልም ሆነ በቤተሰብ የምስራቹን ቃል ለማስፋፋት ቃል እገባለሁ።



Scanned by CamScanner

6. በክርስቲያኖች መካከል ጠብና ክርክርን ከሚያመጡና ቤተ ክርስቲያንን ከሚከፋፍሉ ድርጊቶች ጋር ላለመተባበርና፣ የተሳሳቱትንም ወደ እውነት ለመምራት ቃል እገባለሁ።
7. የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋምና የመተዳደሪያ ደንብ የሚያዘውን ለመፈጸም ቃል እገባለሁ።

### ተጠማቂዎች በዕለቱ አጥማቂ መሪነት በጉባዔው ፊት የሚገቡት ቃል ኪዳን

እኔ ……………………………በጌታ ኢየሱስ ሞት እና ትንሳዔ በማመን አዲስ ሕይወት አግኝቻለሁ። ከዛሬ ጀምሮም ለኃጢአት ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር መሞቴንና በአዲስ ሕይወት ከእርሱ ጋር ለመኖር መነሳቴን በሚገልጽ አንዲት ጥምቀት በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም አምኜ እጠመቃለሁ።

## 3. የጌታ ዕራት መታሰቢያ ሥርዓት

### 3.1 የጌታ እራት ምንነትና አስፈላጊነት

የጌታ እራት የክርስቶስ ሞትና የአዲስ ኪዳን የቃል ኪዳን መታሰቢያ ነው። ክርስቶስ ወደ ሞት ከመሄዱ በፊት በመስቀል ላይ ለሚሰቀለው ሥጋውና ለሚፈሰው ደሙ መታሰቢያ እንዲሆን ሲል የሰጠው ትዕዛዝ ነው። ምዕመናን ሞቱንና ትንሳዔውን ለመናገር ቃል የሚገቡበት ሥርዓት ነው። ደግሞም አማኞች እርስ በርስ ኅብረት የሚያደርጉበትና ከጌታ ጋር በእግዚአብሔር መንግሥት ወደፊት ለሚኖራቸው ሰማያዊ እራት ምሳሌ የሚሆን ሥርዓት ነው።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በወንጌላት ውስጥ ባዘዘው መሰረት (ማቴ. 26:26 - 29፤ ማር. 14:22 - 25፤ ሉቃ. 22:17 - 20) የጌታ ዕራት የክርስቶስን ስቃይና ሞት፣ ለኃጢአታችንም ስርየት ያፈሰሰውን ደም የምናስታውስበት የአዲሱ ኪዳን መታሰቢያና ከክርስቲያኖች ጋር እርስ በርስ የሚኖረን ኅብረት መግለጫ እንደሆነ የቃለ ሕይወት ቤተ



Scanned by CamScanner

ክርስቲያን ታምናለች፡፡

"ፅዋንም ከተቀበለ በኋላ አመስግኖም፡- ይህን እንካችሁ በመካከላችሁ ተካፈሉት፤ እላችኋለሁና የእግዚአብሔር መንግሥት እስክትመጣ ድረስ ከአሁን ጀምሮ ከወይኑ ፍሬ አልጠጣም አለ፡፡ እንጀራንም አንስቶ አመስገነ፤ ቆርሶም ሰጣቸውና ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን ለመታሰቢያ አድርጉት አለ፡፡ እንዲሁም ከዕራት በኋላ ፅዋውን አንስቶ እንዲህ አለ፤ ይህ ፅዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፡፡" (ሉቃ. 22፡17 - 20)

ሐዋርያትም በመስቀል ላይ የተፈጸመውን የክርስቶስን የቤዛነት ሥራ ለማስታወስ ሥርዓቱን ይፈጽሙ እንደነበርና ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለ ሥርዓቱ አፈጻጸም መመሪያ እንደሰጠ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፏል፡፡ (ሐዋ. 2፡42፤ 1ቆሮ. 10፡16 - 17፤ 1ቆሮ. 1፡17 - 34)፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን የእምነት አቋም በተደነገገው መሰረት የጌታ ዕራት መታሰቢያ ሥርዓት ቢዘገይ በወር አንድ ጊዜ መፈጸም አለበት፡፡

## 3.2 የጌታ ዕራት አዘገጃጀት

3.2.1 የጌታ እራት በሩጫና በቸልተኛነት ሳይሆን ህብስቱም ሆነ ጽዋው ከቤተ ክርስቲያን ዲያቆናት በተመረጡ እናቶች ወይም ኃላፊነት ለመውሰድ ብቁ በሆኑ የሴቶች አገልግሎት አስተባባሪዎች በንፅህናና በክብር ይዘጋጃል፡፡

3.2.2 ኅብስቱ ቂጣ ወይም ዳቦ ተቆራርሶ ቢዘጋጅ መልካም ሲሆን፤ የጽዋው ዝግጅት ደግሞ ከአልኮል ነፃ በሆነ የወይን ጭማቂ ወይም ከንፁህ ማር ወይም ሌላ መጠጥ በጥንቃቄ መዘጋጀት ይኖርበታል፡፡

3.2.3 በተቻለ መጠን ጽዋው የሚቀርብበት ዕቃ በበቂ ሁኔታ መዘጋጀትና ንጹህ መሆን ይኖርበታል፡፡ ምናልባት በበቂ ሁኔታ ማዘጋጀት ካልተቻለም በፍጥነት ተሰብስቦና ታጥቦ እንደገና መቅረብ ይችላል፡፡



Scanned by CamScanner

## 3.3 የጌታ እራት አፈጻጸም ሥርዓት

3.3.1 የጌታ እራት ቀን ከመድረሱ አንድ ሳምንት በፊት ምዕመናን ተዘጋጅተው እንዲመጡ ማሳሰብ፤

3.3.2 ቤተ ክርስቲያን እገዳ ካላደረገች በስተቀር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስሙ እንድናደርገው ያዘዘው ሥርዓት ስለሆነ የቤተ ክርስቲያን አባላት የጌታን እራት ሁል ጊዜ መውሰድ አለባቸው።

3.3.4 በቅድስና ጉድለት ወይም በስነ ምግባር ችግር የሚገኙ ሰዎች የጌታን እራት መውሰድ ስለሌለባቸው ራሳቸውን አስቀድመው እንዲመረምሩ ጥብቅ ማሳሰቢያ ሊሰጣቸው ይገባል። ጌታ ኢየሱስን እንደግል አዳኛቸው አድርገው ያልተቀበሉም ከእራቱ ሊካፈሉ እንደማይገባ ማስጠንቀቂያ ሊሰጣቸው ይገባል።

3.3.5 በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው የተለየ ሁኔታ ካልተፈጠረ በስተቀር ሥርዓቱ የሚፈጸመው በወር አንድ ጊዜ ሲሆን ወር በገባ በመጀመሪያው እሁድ ይሆናል።

## 3.4 የጌታ እራት መታሰቢያ ሥርዓት አፈጻጸም ቅደም ተከተል፤

3.4.1 ፕሮግራሙ በጸሎት ይጀመራል፤

3.4.2 ሥርዓቱን የሚያስፈጽሙ የቤተ ክርስቲያን መሪ/አገልጋይ ከ1ቆሮ. 11፡17 — 34 ያለውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንብቦ አጭር መግለጫ ይሰጣል፤

3.4.3 የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ የሚያስታውስ መዝሙር ይዘመራል፤

3.4.4 ኅብስቱና ፅዋውን በዕለቱ የሚያቀርቡ የተመደቡ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ይጠራሉ፤

3.1.4.1 የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ ከ1ቆሮ. 11፡23 - 24 ክፍል ካነበበ በኋላ ኅብስቱ ይታደላል።



Scanned by CamScanner

"ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ ተቀብያለሁና ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠባት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንስቶ አመሰገነ፣ ቆርሶም፣ እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።"

ምዕመናኑም ተጠባብቀው በጸሎት መንፈስ በአንድ ላይ ኅብስቱን ይወስዳሉ።

3.1.4.2 መሪው ከ1ቆሮ. 11፡25 - 26 ያለውን ክፍል ካነበበ በኋላ ፅዋው ይታደላል፤

"እንደዚህም ከእራት በኋላ ፅዋውን ደግሞ አንስቶ፡- ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤ በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፣ ይህን ፅዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።"

ምዕመናኑም በመጠባበቅ በአንድ ላይ ፅዋውን ይወስዳሉ።

3.1.5 የዕለቱ ፕሮግራም በምሥጋና ጸሎት ይጠቃለላል።

# 4. የጋብቻ ሥርዓት

## 4.1 የጋብቻ ምንነት፡-

ጋብቻ በእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ በዔደን ገነት ውስጥ በአንድ ወንድና በአንድ ሴት መካከል እግዚአብሔር ራሱ የመሰረተው ቅዱስና ክቡር ተቋም ነው። (ዘፍ. 21፡8፤ 22 - 25)።

ጋብቻ የሚመሰረተው በእግዚአብሔር ምሪት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነትና በተጋቢዎቹ መፈቃቀድና በዕድሜ ዘመናቸውም ሁሉ አንድ ሥጋ ለመሆን በቤተ ክርስቲያን አመራር በሚካሄድ የቃል ኪዳን ሥነ ሥርዓትና ሁለቱ ተጋቢዎች በእግዚአብሔርና በጉባኤው ፊት በሚገቡት ዕኑ ቃል ማረጋገጫነት እንደሆነ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ታምናለች።



Scanned by CamScanner

ቅዱስ ጋብቻ በክርስቶስና በቤተ ክርስቲያን መካከል ያለውን የፍቅር፣ የመታዘዝና የትስስር ምስጢር የሚያመለክት ምሳሌ ስለሆነ ሁለቱ ተጋቢዎች ትዳራቸውን በመዋደድና በመከባበር ሊመሩት ይገባል። (ኤፌ. 5፡21 - 30)።

ጋብቻ ሁለቱ ተጋቢዎች አንድ ሥጋ በመሆን ተጣምረው በቅድስናና በመደጋገፍ የሚኖሩበትና "ብዙ ተባዙ..." በማለት እግዚአብሔር አምላካችን የሰጠውን መለኮታዊ መመሪያ ተግባራዊ በማድረግ ዘርን የማፍሪያ መንገድም ነው (ማቴ. 19፡4 — 6፤ ኤፌ. 5፡31፤ ዕብ. 13፡ 4)።

### 4.2 የጋብቻ ቅድመ ዝግጅት፦

4.2.1 ዕጩ ተጋቢዎች ቢያንስ ከ6 ወራት በፊት ለቤተ ክርስቲያን ስምምነታቸውን ማስታወቅ ይኖርባቸዋል።

4.2.2 ዕጩዎቹ በአማካሪ ኮሚቴ ወይም በመጋቢው አማካኝነት ራሳቸውን በቅድስና እንዲጠብቁ፣ በሥጦታዎች በመደለል ምንም እንዳይወስኑ፣ ያለ ዕድሜአቸውም ወደዚህ ውሳኔ እንዳይደርሱ፣ ወደ ውሳኔ የደረሱ እንደሆነም ኤች አይ ቪ ኤድስ ምርመራ እንዲያደርጉ ጭምር ምክር ሊያገኙ ይገባል።

4.2.3 አማካሪ ኮሚቴው ዕጩዎቹ ክርስቲያን መሆናቸውን በቃለ መጠይቅም ሆነ በምስክርነት ማረጋገጥ ይኖርበታል።

4.2.4 በሥርግ ዕለት የሚለበሱ የሙሽሮች፣ የሚዜዎችና የአጃቢዎች ልብሶች እግዚአብሔርን የሚያስከብሩ ሰዎችን የማያሰናክሉና የቤተ ክርስቲያንን መድረክ የሚመጥን አግባብነት ያላቸው እንዲሆኑ በቤተ ክርስቲያን ትምህርትና መግለጫ ሊሰጥ ይገባል።

4.2.5 ተጋቢዎች ሚዜዎቻቸውን ሲመርጡ ክርስቲያን መሆናቸውን አስቀድመው እንዲያረጋግጡ በቤተ ክርስቲያኒቱ መመከር አለባቸው። በዝምድናና በሌሎች ምክንያቶች ክርስቲያን ያልሆኑ ሚዜዎች ቢመረጡ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ባለማወቅና እያወቁም በመጣስ ሊያበላሹ ስለሚችሉ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።



Scanned by CamScanner

4.2.6 በቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ወይም መጋቢው በኩል የቅድመ ጋብቻ ጥንቃቄና የትዳር ሕይወት ትምህርት ይሰጣል።

4.2.7 በጋብቻ ዕለት ስለሚከናወኑ የቤተ ክርስቲያን ሥርዓቶች አጭር ሥልጠና ለተጋቢዎች ይሰጣል። ለምሳሌ፡- የሻማ ማብራት ሥርዓት፣ የቀለበት ልውውጥ፣ የሙሽሮች አቋቋም ግራ ሊጋቡ አይገባም።

## 4.3 የጋብቻ ሥርዓት አፈጻጸም ቅደም ተከተል

4.3.1 የፕሮግራሙ መሪ፣ መጋቢው ወይም ቤተ ክርስቲያን የምትወክለው የቃል ኪዳን አስፈጻሚ አገልጋይ፣ መልእክት አቅራቢውና መዘምራን አስቀድመው ቦታቸውን ይይዛሉ፤

4.3.2 ሙሽሮች ሲገቡ የፕሮግራሙ መሪ ጉባዔው ቆሞ በዝማሬ እንዲቀበላቸው ያደርጋል፤

4.3.3 ሙሽሮቹ ቦታቸውን እንደያዙ መጋቢው ወይም የቃል ኪዳን አስፈጻሚው የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ ሙሽሮችንና ጉባዔውን፣ እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት ፕሮግራሙን በጸሎት ይከፍታል፤

4.3.4 በፕሮግራም መሪው አማካኝነት አንድ የጉባዔ መዝሙር ይዘመራል፤

4.3.5 መዘምራን ሁለት መዝሙሮች ያቀርባሉ፤

4.3.6 ከቃለ እግዚአብሔር መልእክት ይቀርባል። (ቢቻል የመልእክቱ ጊዜ ከሠላሳ ደቂቃ ባይበልጥ መልካም ነው።)

4.3.7 የቃል ኪዳን ሥርዓት ይፈጸማል፤

የጋብቻውን ቃል ኪዳን የሚያስፈጽመው አገልጋይ ሙሽሮቹ ፊት ለፊት እንዲቆሙ ይጋብዛቸዋል። ሙሽራው የሚቆመው ከሙሽራይቱ በስተግራ ይሆናል። በሚከተለው ቅደም ተከተል መሠረትም የጋብቻ አስፈጻሚው ሥርዓቱን ይመራል።



Scanned by CamScanner

## ወዳጆች ሆይ!

1. ዛሬ በእግዚአብሔርና በእናንተ ፊት የቆሙትን እነዚህን ሁለት ሙሽሮች ወንድማችን ________ እና እህታችን ________ በቅዱስ ክርስቲያናዊ ጋብቻ ለማጣመር እዚህ ተገኝተናል። ጋብቻ በእግዚአብሔር የታቀደና የተመሠረተ ቅዱስ ተቋም ነው። ጋብቻ ክቡር መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ያረጋግጥልናል። ጋብቻ የተቀደሰ የቤተሰብ ተቋም የሚመሰረትበት ስለሆነ፤ ባልና ሚስት የቤተሰባቸውን አባላት በሚገባ ለማስተዳደርና በእግዚአብሔር መንገድ ለመምራት፣ በእውነተኛ መረዳዳትና መጽናናት፤ በፍቅር፣ በአንድነትና በትዕግሥት እርስ በርሳቸው ለመኖር ኃላፊነት የሚቀበሉበት አደራ ነው። ስለዚህ ይህን ክቡርና ቅዱስ የሆነ ሥርዓት ለመፈጸም ሙሽራውና ሙሽራይቱ ቃል ኪዳን ይገባሉ።
2. ሙሽሮች በቀኝ እጆቻቸው ይጨባበጣሉ።
3. ሙሽሮች የሚገቡት ቃል ኪዳን፦

***ሙሽራው የሚገባው ቃል ኪዳን፦***

እኔ ________ አንቺን ________ የቃል ኪዳን ሚስቴ እንድትሆኚ ፈቅጄ ሳገባሽ ሞት እስኪለየን ድረስ በደስታና በኃዘን፣ በጤንነትና በበሽታ፣ በሃብትና በድህነት ጊዜ ሁሉ አፍቃሪና ታማኝ ባል ልሆንሽ በእግዚአብሔርና በዚህ ጉባዔ ፊት ቃል ኪዳን እገባለሁ። ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳኝ

***ሙሽራይቱ የምትገባው ቃል ኪዳን፦***

እኔ ________ አንተን ________ የቃል ኪዳን ባሌ እንድትሆን ፈቅጄ ሳገባህ ሞት እስኪለየን ድረስ በደስታና በኃዘን፣ በጤንነትና በበሽታ፣ በኃብትና በድህነት ሁሉ ታማኝና ታዛዥ ሚስት እንደምሆንልህ በእግዚአብሔርና በዚህ ጉባዔ ፊት ቃል እገባለሁ። ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳኝ።



Scanned by CamScanner

4. ጸሎት ከተደረገ በኋላ ሙሽሮች ለሚከተሉት ጥያቄዎች የማረጋገጫ ቃል ከሰጡ በኋላ ቀለበት ይለዋወጣሉ። (ቀለበት ያልተዘጋጀ ከሆነ እንደ አካባቢው ሁኔታ ሥርዓቱ ሊፈጸም ይችላል።)

*ለሙሽራው ጥያቄ*

ወንድም ____________ በዚህ ቀለበት ምልክት ይህቿን እህታችንን ____________ ስታገባ ሞት እስኪለያችሁ ድረስ እንደ ራስህ አድርገህ እንደምትወዳት ለመግለጽ ፈቃደኛ ነህን?

*ለሙሽራይቱ ጥያቄ*

እህት ____________ በዚህ ቀለበት ምልክት ይህን ወንድማችንን ____________ ስታገቢው ሞት እስኪለያችሁ ድረስ እንደ ራስሽ አድርገሽ እንደምትወጂው ለመግለጽ ፈቃደኛ ነሽን?

5. ጉባዔው ይቆማል፤ የጋብቻ ሥርዓት አስፈጻሚውም እንደሚከተለው ጋብቻውን ያጸናል፤

በተቀደሰው ሕጋዊ ጋብቻ ለመጣመር በእግዚአብሔርና በዚህ ጉባዔ ፊት ስለተስማማችሁ ባልና ሚስት መሆናችሁን በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም እኔ ____________ አስታውቃለሁ። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው (ማቴ. 19:6)።

6. ሙሽራውና ሙሽራይቱ ቀደም ብሎ በተዘጋጀላቸው ስፍራ ተንበርክከው ጸሎትና ቡራኬ ይደረግላቸዋል።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ፤ ይጠብቃችሁም፤
እግዚአብሔር ፊቱን ያብራላችሁ፣ ይራራላችሁም፤
እግዚአብሔር ፊቱን ወደናንተ ያንሳ፣ ሰላምንም ይስጣችሁ፤
በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም።
አሜን።



Scanned by CamScanner

ጉባኤው ይቀመጣል፡፡

7. የፊርማ ሥነ ሥርዓት ይፈጸማል፤

የሙሽራው ፊርማ፣ የሙሽራይቱ ፊርማ፣ የምስክሮች ፊርማና የቤተ ክርስቲያን መሪው ወይም የቃል ኪዳን አስፈጻሚው ፊርማ እንደ ቅደም ተከተሉ ይከናወናል፡፡ የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ የጋብቻ የምስክር ወረቀቱም በቤተ ክርስቲያን መሪው/በቃል ኪዳን አስፈጻሚው አማካኝነት ለሙሽሮች ይሰጣል፡፡

8. የሻማ ማብራት ፕሮግራም፤

በማቴ. 5፡ 14 — 15 ላይ እንደተጻፈው ሙሽሮቹ ቀደም ሲል በየግላቸው ለክርስቶስ ሲያበሩ ነበር፡፡ ከዛሬ ጀምሮ ደግሞ በአካባቢያቸውና በቤተሰቦቻቸው መካከል በጋራ ለማብራት መስማማታቸውን ለማሳየት የየራሳቸውን የበራ ሻማ አጥፍተው የጋራቸውን አንዱን ሻማ ይለኩሳሉ፡፡

9. የቤተ ክርስቲያን መሪው ወይም የቃል ኪዳን አስፈጻሚው አገልጋይ ለሙሽሮቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ስጦታ ያበረክትላቸዋል፡፡

“ይህን የእግዚአብሔርን ቃል ለኑሮአችሁና ለሕይወታችሁ መሪ እንዲሆን አንብቡት፡፡”

ሙሽራው ከሙሽራይቱ በስተቀኝ በመዞር ወደ ስፍራቸው ይመለሳሉ፡፡

4.1.8 መዘምራን የመጨረሻውን ክፍል ሁለት መዝሙሮች ያቀርባሉ ወይም በዝማሬ አምልኮ መሪዎች እየተመራ ጉባዔው ይዘምራል፡፡

4.1.9 የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ/የዕለቱ ፕሮግራም መሪ የዕለቱን ፕሮግራም በጸሎት ያጠቃልላል፡፡



Scanned by CamScanner

## 5. ሕጻናትን ለእግዚአብሔር የማስረከብ ሥርዓት

### 5.1 ትርጉምና አስፈላጊነት

ሕጻናት የእግዚአብሔር ስጦታ፣ የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ናቸው፤ (መዝ. 127፡3)፣ "እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን።" ኢያሱ 24፡15 በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በተመላለሰበት ዘመን ሰዎች ሕጻናቶቻቸውን ወደ እርሱ በማቅረብ እንዲባርካቸው ይጠይቁት ነበር።

"እንዲዳስሳቸውም ሕጻናትን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም ያመጧቸውን ገሰጹአቸው። ኢየሱስ ግን አይቶ ተቆጣና ሕጻናትን ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሏቸው፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ሕጻን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አላቸው። አቀፋቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው" (ማር. 10፡13 - 16)

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በዓመቱ ውስጥ የሚወለዱት የቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ልጆች ወደ እግዚአብሔርና ወደ ጉባዔው ፊት ቀርበው እንዲጸለይላቸው በዕምነት አቋሟ ውስጥ ደንግጋለች። ስለሆነም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ለዚህ ፕሮግራም በዓመት ውስጥ በምትይዛቸው ሦስት ፕሮግራሞች ምዕመናን በሚመቻቸው በአንደኛው ፕሮግራም ውስጥ ቀደም ብለው ፕሮግራም አስይዘው ሕጻናትን ወደ እግዚአብሔር ፊት ማቅረብ ይኖርባቸዋል። በኢሳይያስ 8፡18 "እነሆ እኔና እግዚአብሔር የሰጠኝ ልጆች… ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክትና ተዓምራት ነን፤" ስለሚል ወላጆች በየጊዜው የሚወልዷቸውን ሕጻናት ለእግዚአብሔር ማስረከቡ በረከት እንደሆነ ማስተማሩ ተገቢ ነው። ይህ ሥርዓት የሚፈጸመው በእሁድ የአምልኮ ፕሮግራም ላይ ሲሆን የሕጻኑ/ኗ እናትና አባት ሁለቱም መገኘት ይኖርባቸዋል። (1ሳሙ. 1፡26)



Scanned by CamScanner

5.2 ሕጻናትን ለእግዚአብሔር የማስረከብ ሥርዓት ፕሮግራም ቅደም ተከተል፡-

5.2.1. በዕለቱ ሕጻናትን ለእግዚአብሔር የሚያስረክቡት ወላጆች ከሕጻናቱ ጋር የተዘጋጀውን ቦታ ይይዛሉ፤

5.2.2. የልጆች አገልግሎት አስተባባሪው ወይም ፕሮግራሙን በጸሎት በመጀመር ሕጻናትን ለእግዚአብሔር ስለ ማስረከብ መግለጫ ይሰጣል፤

5.2.3. ሥርዓቱን ለማስፈጸም ቤተ ክርስቲያን የወከለችው መሪ የሕጻናቱን ወላጆች ወደ ጉባዔው ፊት ለፊት በመጋበዝ ይህንን ቃል ኪዳን በጋራ እንዲገቡ ያደርጋል፤

*የዚህ/ የእነዚህ ሕጻናት ወላጆች*

*(አቶ____________ እና ወ/ሮ ____________) ዛሬ ____________ ቀን ____________ ዓ.ም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ልጅ/ልጆች ለማስረከብ በእግዚአብሔርና በዚህ ጉባዔ ፊት ቆመዋል።*

*ወላጆች ሆይ ይህንን ሕጻን/እነዚህን ሕጻናት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በቤትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በእንክብካቤና በፍቅር ለማሳደግ ቃል ትገባላችሁን?*

5.2.4. ጉባዔው እንደቆመ ሥርዓቱን የሚያስፈጽመው አገልጋይ ሕጻኑን/ሕጻኗን/ ሕጻናቱን ከወላጆቹ ተቀብሎ በማቀፍ በጸሎት ለእግዚአብሔር አሳልፎ ይሰጣል። (የሕጻናቱ ቁጥር በርካታ ከሆነ ሌሎች ሽማግሌዎችና አገልጋዮች ተጋብዘው ሕጻናቱን እንዲያቅፉ ይደረጋል፤ ወይንም በሕጻናቱ ላይ እጆቻቸውን ዘርግተው ይጸልዩላቸዋል።)

*የቡራኬ ጸሎት*

*"እግዚአብሔር ይባርካችሁ ይጠብቃችሁም*
*እግዚአብሔር ፊቱን ያብራላችሁ ይራራላችሁም፤*
*እግዚአብሔር ፊቱን ወደናንተ ያንሳ፤*
*ሰላምንም ይስጣችሁ" (ዘኁ. 6፡24 - 26)።*
*በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም፤*
*አሜን።*



Scanned by CamScanner

5.2.5 በመጨረሻም ለሕጻናቱ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ የልደት ሰርተፊኬትና ለብላቴናው እንደ አመቺነቱ መጽሐፍ ቅዱስ ታዘጋጅቶ በቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ/ተወካይ አማካይነት ተሰጥቶ ሥርዓቱ ይጠናቀቃል።

## 6. የቀብር ሥርዓት

### 6.1 የሞት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምንነት

የሥጋ ሞት ለሰው ልጆች ሁሉ ባለመታዘዝ ኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር የተሰጠ መለኮታዊ ትዕዛዝ ነው (ዘፍ. 2፡17)። እግዚአብሔር አዳምን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቅ ዛፍ አትብላ ብትበላ ሞትን ትሞታለህ ብሎ ከከለከለው ዛፍ በመብላቱ ኃጢአትንና ሞትን ሊያመጣ ችሏል (ዘፍ. 3፡19፤ ሮሜ. 5፡12)።

ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የሚያምን ክርስቲያን ሁሉ ከሞት ወደ ሕይወት የተሸጋገረ መሆኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐ. 5፡24 መሠረት ማረጋገጫ ሰጥቶናል።

ሞት እውነተኛ ክርስቲያንን ወደ እግዚአብሔር ዘላለማዊ መኖሪያ ወደ ገነት የሚወስድ እንጂ ወደ ዘለዓለም ኩነኔ የሚያሸጋግር ስላይደለ የሟች ቤተሰቦችና ወዳጆች ሁሉ በአምላካዊው የተስፋ ቃል መጽናናት ይገባቸዋል። ደግሞም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም"። (ዮሐ. 11፡25 - 26) በማለት ዕኑ የተስፋ ቃል ስለሰጠን ስለሞተው ሰው አምርረን ማዘን እንደሌለብን ያስገነዝበናል (2 ቆሮ. 5፡1፣ 1፣ ተሰ. 4፡13 - 18)።

ቅዱስ ዳዊትም፣ "የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው፣" (መዝ.116፡15) በማለት ሕያው የሆነ የተስፋ መልህቅ ጥሎልናል።

ስለሆነም ምንም እንኳን ወገናችን በሥጋዊ ዕረፍት በሞት ሲለየን የሚያሳዝነን ቢሆንም ተስፋ እንደሌላቸው ሰዎች በመሪር ኃዘን ውስጥ



Scanned by CamScanner

ስጥሞ በባህላዊ የልቅሶ ልምድና ባህላዊ ሙሾ ራስን መጉዳት ተገቢ አይደለም፡፡

## 6.2 የቀብር ሥርዓት አፈጻጸም ፕሮግራም፡-

የቀብር ሥርዓት አፈጻጸም የአካባቢውን ሁኔታና ወቅቱን ያገናዘበ ሆኖ በሚከተለው ሁኔታ ይፈጸማል፤

ሀ. የሟች አስከሬን በሚወጣበት ቤት የሚደረግ ሥርዓት፤

1. በቤተ ክርስቲያኒቱ መጋቢ ወይም የተወከለ አገልጋይ አማካኝነት ጸሎት ይደረጋል፤
2. ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል ተነብቦ አጭር የመልእክት ጊዜ ይኖራል፤
3. ሁለት ያህል መዝሙሮች ተዘምረው ጸሎት ከተደረገ በኋላ አስከሬኑ ከቤት ይወጣል፡፡

ለ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚደረግ ሥርዓት፤

1. አስከሬኑ ከጉባኤው ፊት ለፊት እንዲያርፍ ይደረጋል፤
2. የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ (መጋቢ) ጸሎት ያደርጋል፤
3. መዘምራን ሁለት መዝሙር ያቀርባሉ፤
4. ከቃለ እግዚአብሔር መልእክት ይቀርባል (መልእክቱ ከሃያ ደቂቃ ባይበልጥ መልካም ነው፡፡)
5. መዘምራን አንድ መዝሙር አቅርበው ፕሮግራሙ በጸሎት ያበቃል፡፡

ሐ. በቀብር ቦታ የሚደረግ ሥርዓት፡-

1. ጸሎት ይደረጋል፤
2. ከመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ክፍል ይነበባል፤ (የመልእክቱ ይዘት ስለ ዘለዓለማዊ ሞትና ስለ ትንሳኤ ለቀብር የተገኙ ኃዘንተኞችም በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሚኘው የዘለዓለም ሕይወት እንዲያስቡ የሚጋብዝ ሆኖ ከ10 ደቂቃ መብለጥ አይኖርበትም፡፡)



Scanned by CamScanner

3. የአስከሬኑ ግብዓተ መሬት ሥርዓት ሲፈጸም ስለ ትንሣኤ የሚናገሩ አዝማቾች ይዘመራሉ፡፡
4. ሁኔታዎች የተመቻቹ ከሆነ የሟች የሕይወት ታሪክ ይነበባል፡፡
5. የሐዋርያት ጸሎት ተደርጎ ሥርዓቱ ይጠናቀቃል፡፡

(እንደ አመቺነቱ ከዚህ በላይ በተገለጹት ሦስት ስፍራዎች ወይንም ሁኔታው በሚፈቅደው መሠረት ብቻ የቀብር ሥርዓት ፕሮግራሙ ሊፈጸም ይችላል፡፡ ከዚህ ውጪ በሆነ መንገድ ከአካባቢ ባህል የተወሰዱ እና በልማድ የሚተገበሩ ልዩ ልዩ መነፈሳዊ መልክ ያላቸው ድርጊቶችን በቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት በሚፈጸም የቀብር ሥርዓት ላይ እንዳይተገበሩ መጠንቀቅ ይገባል፡፡)

በቀብር ሥርዓት ወቅት ከሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አንዱን ወይንም ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን መርጦ ማንበብ ይቻላል፡፡ (ዘፍ. 3፡19፤ ዮሐ. 5፡24 — 25፣ 11፡24 — 26፤ ኢዮብ. 19፡25 — 27፤ ኢሳ. 38፡1፤ 1ቆሮ. 15፡1 — 57፤ 2ቆሮ. 5፡1 — 5፤ 1ተሰ. 4፡ 13 — 18፤ ራእይ 20፡11 — 15፣ 21፡1 — 5)፡፡

## 7. የሽማግሌዎች ሹመት ሥርዓት

### 7.1 የሽማግሌዎች አገልግሎት ትርጉምና አስፈላጊነት፡-

የሽምግልና አገልግሎት እግዚአብሔር ለቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የሰጠው ስጦታ ነው፡፡ ቤተ ክርስቲያን ስትቋቋም ሐዋርያት ለሽምግልና አስተዳደር አገልግሎት የተጠሩትንና የተመረጡትን ከፆሙና ከጸለዩ በኋላ አደራና ኃላፊነት እየሰጡአቸው ይሾሙአቸው እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጽፏል፡፡

"...በዚያችን ከተማ ወንጌልን ሰብከው እጅግ ደቀ መዛሙርት ካደረጉ በኋላ የደቀ መዛሙርቱን ልብ እያጸኑ በሃይማኖትም ጸንተው እንዲኖሩ እየመከሩና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በብዙ መከራ እንገባ ዘንድ ያስፈልገናል እያሉ ወደ ልስጥራን ወደ ኢቆንዮንም ወደ አንጾኪያም ተመለሱ፡፡ በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን



Scanned by CamScanner

ከሾሙላቸው በኋላ ጦመውም ከጸለዩ በኋላ ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡአቸው" (ሐዋ. 14:19 — 23)።

የሽምግልና አገልግሎት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም የተዋጀችውን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በታማኝነት ማስተዳደርና መምራት ሲሆን ለምዕመኑም አርአያና የፍቅርም ምሳሌ መሆን እንደሚያስፈልግ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡ (ሐዋ. 20:17 — 28፤ 1ጴጥ. 5:1 — 5)።

ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚሾም ሽማግሌ ማሟላት የሚገባውን የብቃት መስፈርት በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዝርዝር ተመልክቷል። (1ጢሞ. 3፡ 2 — 7፤ ቲቶ. 1:5 - 9)።

የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ምርጫ የሚጸናው ቤተ ክርስቲያኒቱ የምትሰይመው አስመራጭ ኮሚቴ ከላይ በቀረቡት መስፈርቶች መሰረት አጣርቶ ካቀረባቸው ዕጩዎች መካከል ሆኖ የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የምርጫ አፈጻጸም መመሪያ በሚያዘው መሰረት የምዕመናኑ ጉባዔ በአብላጫ ድምፅ ሲመርጣቸው ይሆናል።

የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ዋና ዋና አገልግሎቶች እና ዝርዝር ኃላፊነቶች በቤተ ክርስቲያኒቱ የመተዳደሪያ ደንብ ክፍል ሁለት አንቀጽ 10 ላይ ቀርቧል።

## *7.2 የሽማግሌዎች የሹመት ሥርዓት አፈጻጸም ፕሮግራም ቅደም ተከተል*

7.2.1 የሽማግሌዎች ምርጫ የሚካሄደው ከዕሁድ ዕለት አምልኮ በኋላ መራጭ አባላት ወደ ኋላ እንዲቀሩ ተደርጎ ይሆናል።

7.2.2 የሽማግሌዎች ሰብሳቢ አስመራጭ ኮሚቴዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ ካለ በኋላ አስመራጮችን ለምርጫ ዝግጅት ኮሚቴ አስተዋውቆ ስፍራውን ለአስመራጮች ይለቃል።

7.2.3 የምርጫ አመቻች ኮሚቴው በበኩሉ አስመራጭ ኮሚቴውን እንኳን ደህና መጣችሁ ካለ በኋላ ዕጩዎችን ለጉባዔው አስተዋውቆ ስፍራውን ለአስመራጮች ይለቃል።



Scanned by CamScanner

7.2.4 የአስመራጭ ኮሚቴው ምርጫውን በምርጫ መመሪያው መሰረት ካስፈጸመ በኋላ ውጤቱን ለህዝቡ ይፋ ያደርጋል።

7.2.5 በምርጫ መመሪያው ላይ በተደነገገው መሰረት የኃላፊነት ድልድል ይደረጋል።

7.2.6

7.2.7 ለቀድሞዎቹ ሽማግሌዎች ጉባኤው ቆሞ ይጸልይላቸዋል። የምርጫው ውጤት ተገልጾ ሕዝቡ እንደቆመ አዲሶቹ ሽማግሌዎች በታማኝነትና በቅንነት ጌታንና ምዕመኑን ለማገልገል መስማማታቸውን ይገልጻሉ። ከዚያም አስመራጭ ኮሚቴው ሰብሳቢ አማካኝነት ቃል ኪዳን ከገቡ በኋላ በጉባኤው ፊት ተንበርክከው የቀድሞዎቹ ሽማግሌዎች እጃቸውን በመጫን ይጸልዩላቸዋል።

* የቀድሞዎቹ ሽማግሌዎች በዚሁ ሥነ ሥርዓት ላይ ወይም በሌላ ምቹ ጊዜ የሰጡትን አገልግሎት የሚገልጽ የምስጋና የምስክር ወረቀት ከተቻለም የአገልግሎት መታሰቢያ የመጽሐፍ ቅዱ ስጦታ ተበርክቶላቸው በክብር ከአገልግሎቱ ይሰናበታሉ።

## አዲሶቹ ተሿሚ ሽማግሌዎች የሚገቡት ቃል ኪዳን

1. እግዚአብሔር ለዚህ ታላቅ አገልግሎት እንደሾመኝ አምናለሁ፤
2. መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠኝ ጥበብና ራእይ ምዕመኑን በፍቅርና በርህራሄ ላስተዳድር ቃል እገባለሁ፤
3. በምዕመናን መካከል መከፋፈልንና መለያየትን ከሚፈጥሩ ድርጊቶች ለመራቅና የተሳሳቱትንም ወደ ትክክለኛው መንገድ ለመምራት ቃል እገባለሁ፤
4. ምዕመኑ በእግዚአብሔር ቃል እንዲያድግና እንዲጎለብት፣ አዳዲስ ክርስቲያኖችም በእምነታቸው እንዲጸኑ የሚያስችለውን ተገቢ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ ቃል እገባለሁ፤
5. ከስህተት ትምህርት ልምምዶች ራሴንና ምዕመኑን ለመጠበቅ ቃል እገባለሁ፤
6. የቤተ ክርስቲያንን ንብረትና ገንዘብ በሥርዓቱና በአግባቡ



Scanned by CamScanner

ለመቆጣጠር ቃል እገባለሁ፤

7. በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋምና የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት ቤተ ክርስቲያኒቱን ልመራና ላስተዳድር ቃል እገባለሁ።

ይህንንም ለመፈጸም እግዚአብሔር ይርዳኝ።
አሜን!

7.2.8 ፕሮግራሙ በጸሎትና በቡራኬ ቃል ይጠናቀቃል።

# 8. የዲያቆናት ሹመት ሥርዓት

## 8.1 መግቢያ

የዲያቆናት አገልግሎት የተጀመረው በመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን የወንጌሉ የምሥራች ቃል እየሰፋ ወደ ክርስትና የሚገባው ሕዝብ ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ ነው፤ (የሐዋ. ሥራ 6፡1 - 6)። ዲያቆናት የእግዚአብሔርን ቤት ሥራ ለመርዳትና ለመደገፍ፣ በሽማግሌዎችና በወንጌላውያን ታጭተው ለከፍተኛ ኃላፊነትና ማዕረግ የሚመረጡ ስለሆነ ትልቅ ጥንቃቄና ጸሎት ያስፈልገዋል። ዲያቆናት የተፈተነውን ራሳቸውን ለእግዚአብሔር ቤት አገልግሎት የሚያቀርቡ የጌታን ሃሳብና ፈቃድ እያገለገሉ የቅዱሳንን ልብ የሚያሳርፉ ታማኝ አገልጋዮች መሆን ይጠበቅባቸዋል።

ለዚህ ታላቅ አገልግሎት የሚታጩ ዲያቆናት ሊኖራቸው የሚገባውን የብቃት መስፈርት በተመለከተ የእግዚአብሔር ቃል በ1ጢሞ. 3፡10 - 11 ዝርዝር አስቀምጧል።

የዲያቆናት ምርጫ የሚጸናው ለዚህ አገልግሎት በሽማግሌዎችና በወንጌላውያን በዕጩነት ከቀረቡት መካከል በጉባዔው አብላጫ ድምፅ ሲያገኙ ነው። የሚመረጡት ዲያቆናት ቁጥር እንደ ቤተ ክርስቲያኒቱ ስፋት ከ7 - 12 ሊደርስ ይችላል።



Scanned by CamScanner

## 8.2 የዲያቆናት አገልግሎትና የሥራ ኃላፊነት፡-

ሀ. ቤተ ክርስቲያንን ለአምልኮና ለልዩ ልዩ መንፈሳዊ ፕሮግራሞች ማዘጋጀት፤

- የጸሎት ቤቱን የውስጥ ይዘት ማስተካከል፣ ጽዳቱንና ውበቱን መጠበቅ፤
- ምዕመናንን ማስተናገድ፤
- የጌታ ራት መታሰቢያ ኅብስትንና ወይኑን ማዘጋጀት፤
- የጥምቀት ሥርዓት ሲካሄድ አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት ማድረግና ተጠማቂዎችን መርዳት፤
- የተለያዩ መንፈሳዊ ፕሮግራሞችንና መስተንግዶዎችን ማስፈጸም፤
- መባ መሰብሰብ፣ መዝግቦና ቆጥሮ ማስረከብ፤
- የቤተ ክርስቲያኒቱን ቋሚና ተንቀሳቃሽ ንብረቶች መንከባከብና መጠበቅ፤
- የቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ እና የአምልኮ አዳራሽ የውስጥ ገጽታ ያማረ እንዲሆን ተገቢውን ጥረት ማድረግ

ለ. የቤተ ክርስቲያንን ማኅበራዊ ጉዳይ በሚመለከት፤

- የታመሙትን፣ የደከሙትን፣ ያዘኑትንና የተቸገሩትን መጎብኘት፣ ማፅናናት፣ መርዳትና የደረሱበትንም ውጤት ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ማሳወቅ፤
- የቀብር ሥርዓትን ቅድመ ዝግጅት ማመቻቸትና ምዕመኑ ኃዘንተኛውን ቤተሰብ እንዲያጽናና ከቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ጋር በመመካከር ማስፈጸም። በምዕመናን ላይ የሚደርሱ ያልተጠበቁ ችግሮችንና አጋጣሚዎችን ለማቃለል ሕዝቡን ማስተባበርና ቀድመው በመገኘት መርዳት፤
- በቤተ ክርስቲያን እና ምዕመናኗ ሊደገፉ የሚገባቸው ችግር አባላትን በማጥናት ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤



Scanned by CamScanner

- ከላይ ከተዘረዘሩት በተጨማሪም ዲያቆናት እግዚአብሔር በሰጣቸው ልዩ ልዩ ሥጦታዎችም ማገልገል ይችላሉ። (ለምሳሌ:- በመስበክ፣ በማስተማር፣ በመዘመር፣ ፕሮግራም በመምራት ወዘተ...)

## 8.3 የዲያቆናት የሹመት ሥርዓት አፈጻጸም ፕሮግራም ቅደም ተከተል

8.3.1 የምርጫው አፈጻጸም ሂደትና ቅደም ተከተል የሽማግሌዎችን የምርጫ አፈጻጸም ሥርዓት የተከተለ ሆኖ የዲያቆናት ምርጫ አመቻችም ሆነ አስመራጮች የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪዎች ይሆናሉ።

# 9. የወንጌል መልዕክተኞች፣ የመጋብያን እና የአስተማሪዎች ሹመት ሥርዓት

## 9.1 መግቢያ:-

"እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት ሌሎችም ነብያት፣ ሌሎቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ" (ኤፌ. 4:11)።

አገልግሎት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ስጦታ ነው። በመሆኑም እግዚአብሔርን ለማገልገል ራሱን የሚሰጥ ሰው ጥሪ ያለውና ከእግዚአብሔር ስጦታን የተቀበለ መሆን አለበት። እግዚአብሔር ስጦታን የሚሰጠው ለእያንዳንዱ እንደፈቀደ ስለሆነ ሰው እንደተሰጠው የጸጋ ስጦታ ማገልገል ይገባዋል። (ሮሜ. 12:3 — 8፤ 1ቆሮ. 12)።

እግዚአብሔር የአገልግሎት ጸጋን በመስጠት ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጣቸውን አገልጋዮች የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥሪአቸውን በጥንቃቄ አረጋግጠውና ለይተው ማወቅና መያዝ ይኖርባቸዋል። ስጦታ እንዳላቸው ያረጋገጡና የተረጋገጠላቸው አገልጋዮችም እግዚአብሔርን በመፍራት፣ በትህትናና በፍርኃት ሊያገለግሉና ሊመላለሱ ይገባል (2ጢሞ. 2:15)።



Scanned by CamScanner

የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በጥሪአቸው መሠረት በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ፈትነው የለዩአቸውን አገልጋዮች የሕይወት ምስክርነት ካጠኑ በኋላ ወደተለዩበት የአገልግሎት አቅጣጫ የጸሎት ቆይታ አድርገው ሊያስማሯቸው ይገባል።

የወንጌል መልእክተኞች በአገር ውስጥና ከአገር ውጭ እንደ ጥሪአቸውና ጸጋቸው የሚላኩ ናቸው። ዋና ተግባራቸውም ወንጌልን ላላመኑት ሰዎች በመመስከር ደቀ መዛሙርት ማድረግ ነው። ይህ አገልግሎት ከሌላው የበለጠ ዋጋ የሚያስከፍል ስለሆነ ለዚህ አገልግሎት ራሳቸውን የሚሰጡ አገልጋዮች ዋጋቸውን ተምነው የሚወጡ መሆን አለባቸው።

መጋቢነት መንጋን የመምራት፣ የመመገብ፣ የመጠበቅና የመንከባከብ ኃላፊነት ነው። የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ እንደሚያስተምረው የእረኞች አለቃ ጌታ ኢየሱስ ስለሆነ ከሁሉም በላይ ለዚህ ተጠሪነት መገዛት ዋነኛ መርህ ሊሆን ይገባል። መጋቢ የሚሆን አገልጋይ የሚመራቸውን ሰዎች መንፈሳዊና ቁሳዊ ኃላፊነት ስለሚሸከም ሰፊ ትከሻ ያለው መሆን አለበት።

አስተማሪነት ሰዎች የማያውቁትን ነገር እንዲያውቁ ማድረግ ነው። ይህ ማለት አስተማሪ ወደ እውነትም ወደ ስህተትም የመምራት ዕድሉ አለው ማለት ነው። ስለዚህም አስተማሪ የሚሆን አገልጋይ የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በማስተማር የሚማሩትን ከስህተት ትምህርት የመጠበቅና ክርስቶስን ወደመምሰል ሕይወት የሚያሳድግ መሆን አለበት።

## 9.2 የሹመት ሥርዓቱ አፈጻጸም ፕሮግራም ቅደም ተከተል

9.2.1 ምዕመናንና አገልጋዮች በሙሉ የሚገኙበት ልዩ ስብሰባ ያዘጋጃል፤

9.2.2 የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ ለጉባኤው የእንኳን ደህና መጣችሁ መልእክት አስተላልፎ ፕሮግራሙን በጸሎት ይከፍታል፤



Scanned by CamScanner

9.2.3 በዕለቱ እንደሚካሄደው የሹመት ሥነ ሥርዓት ከአጥቢያይቱ የበላይ እርከን የሚወክሉ የመርኃ ግብሩ አስፈጻሚዎች ወይም የበላይ እርከን የዘርፍ ተወካዮች (የሚሽን አገልግሎት፣ የመጋቢያን ሥልጠና ክፍል ወይም የሥነ መለኮት ትምህርት አስተባባሪዎች) በእንግድነት ከተገኙ ለጉባዔው በማስተዋወቅ ተገቢውን ስፍራ እንዲይዙ ያደርጋል።

9.2.4 ለሿሚነት የተወከለው አገልጋይ ስለ ዕለቱ ፕሮግራም መግለጫ ይሰጣል፤

9.2.5 ከሁለት ያልበለጠ የጉባኤ መዝሙር ይዘመራል፤

9.2.6 መዘምራን የሚኖሩ ከሆነ የመጀመሪያውን ክፍል ሁለት መዝሙሮች ያቀርባሉ፤

9.2.7 የዕለቱን ፕሮግራም አስመልክቶ የተዘጋጀ ቃለ እግዚአብሔር ይቀርባል፤

9.2.8 የሹመት ሥርዓት ይፈጸማል፤

- ተሿሚዎቹ እንደቆሙ ሿሚው የምክር ቃል ይሰጣል፤
- ጉባዔው ይቆማል፤ ተሿሚዎች ይንበረከካሉ፤
- ሽማግሌዎች እጅ ጭነው ይጸልዩላቸዋል።

9.2.9 ተሿሚ አገልጋዮች ቆመው ቃል ኪዳን ይገባሉ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ አስቀድሞ ለደቀ መዛሙርቱ የታላቁን የወንጌል ተልዕኮ ዓላማ እንዲያስፈጽሙ አደራ ሰጥቷቸው ነበር። (ማቴ. 28፡19 — 20፤ ዮሐ. 21፡15 - 17)።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ለኤፌሶን ሽማግሌዎች በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን በትጋት እንዲጠብቁ የአደራ ቃል እንደተወላቸው ተጽፏል። (የሐዋ. ሥራ 20፡18 - 38)፤ ጢሞቴዎስም ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠውን የጸጋ ስጦታዎች ቸል እንዳይልና በአግባቡ እንዲጠብቅ ሐዋርያው አሳስቦታል፤ (1ጢሞ. 4፡14 - 16)።

በዚሁ መሰረትም ተሿሚዎች ወንጌላውያን ወይንም መጋቢያን (አስተማሪዎች) ወይንም ለሚስዮን ሥራ የሚሰማሩ አገልጋዮች የሚከተለውን ቃል ኪዳን ይገባሉ። ተሿሚዎች ቃል ኪዳን በሚገቡበት



Scanned by CamScanner

ጊዜ ባለትዳር ከሆኑ የትዳር አጋሮቻቸው አብረው ቆመው ቃል ኪዳን በመግባቱ ሂደት ይሳተፋሉ።

1. ለዚህ ታላቅ የቤቱ አገልግሎት እግዚአብሔር እንደጠራኝ፤ ሽክምና ስጦታም እንደሰጠኝ አረጋግጬ የአገልግሎት ጥሪውን በሙሉ ልብ ተቀብያለሁ፤
2. ለተጠራሁበት ታላቅ አገልግሎት ራሴን መስዋዕት አድርጌ ለማቅረብ ቃል እገባለሁ፤
3. እግዚአብሔር ለቤቱ አገልግሎት በጠራኝና በሰጠኝ ስጦታ መሰረት ቤተ ክርስቲያን በምትመድበኝ ቦታ ሁሉ በፍጹም ታዛዥነት ለማገልገል ቃል እገባለሁ፤
4. የወንጌሉን የምስራች ቃል በጊዜውም አለጊዜውም አውጃለሁ፤ ያመኑትንም ለማስተማርና ለማሳደግ ቃል እገባለሁ፤
5. የቤተ ክርስቲያንን አንድነትና ኅብረት ከሚያውኩ ነገሮች ሁሉ ራሴን እጠብቃለሁ፤ ሌሎች የተሳሳቱም ወደ እውነት እንዲመለሱ አስተምራለሁ፤
6. በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋምና የመተዳደሪያ ደንብ መሰረት ለማገልገል ቃል እገባለሁ፤
7. ከእግዚአብሔርና ከቤተ ክርስቲያን የተቀበልኩትን ይህን ትልቅ ኃላፊነትና አደራ በመንፈስ ቅዱስ ኃይልና ብርታት ለመፈጸም ቃል እገባለሁ።

በዚህ ሁሉ እግዚአብሔር ይርዳኝ። አሜን።

9.2.9 ለተሿሚዎች ቤተ ክርስቲያን ያዘጋጀችው የሹመት ደብዳቤ ይሰጣቸዋል፤
9.2.10 ተሿሚዎች አጭር ምስክርነታቸውን ይሰጣሉ፤
9.2.11 መዘምራን የመጨረሻ ክፍል መዝሙር ያቀርባሉ፤
9.1.12 የተሿሚ ቤተሰቦች ይቆሙና የማጠቃለያ ጸሎትና የቡራኬ ቃል ይሰጣል።



Scanned by CamScanner

*እግዚአብሔር ይባርካችሁ፣ ይጠብቃችሁም፤*
*እግዚአብሔር ፊቱን ያብራላችሁ፣ ይራራላችሁም*
*እግዚአብሔር ፊቱን ወደናንተ ያንሳ፣ ሰላሙንም ይሰጣችሁ።*
*በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም*
*አሜን።*

## 10. *የከፍተኛ የሥነ መለኮት ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ምረቃ ሥርዓት*

### *10.1 መግቢያ:-*

እግዚአብሔር በየዘመናቱ ለእርሱ አገልግሎት ተለይተው በቤቱ የሚያገለግሉትን ሰዎች በጠራቸውና በለያቸው ጊዜ ሁሉ የተጠሩበትን አገልግሎት በታማኝነትና በታዛዥነት እንዲፈጽሙ ጥሪውን ለተቀበሉ አገልጋዮች መመሪያና ጥበብ ይሰጣቸው እንደነበር በብሉይና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጽፏል።

#### ሀ. በብሉይ ኪዳን

ሙሴ፣ አሮንና ልጆቹን እና ባስልኤልን ለአገልግሎት ሲለያቸው እንደ ቃሉ መዘጋጀታቸውን ካረጋገጠ በኋላ አዘዛቸው። (ዘጸ. 25:35)።

ንጉሥ ዳዊት በዘመኑ የእግዚአብሔርን ቤት አገልጋዮች በሥነ ሥርዓት ለይቶ አዘጋጃቸው፤ ቀደሳቸውም (1ዜና. 25)።

ንጉሥ ሕዝቅያስም ለእግዚአብሔር ቤት የመረጣቸውን አገልጋዮች ሰብስቦ መመሪያ ሰጥቶ አሰማራቸው (2ዜና. 29:11)።

#### ለ. በአዲስ ኪዳን፤

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሦስት ዓመታት ያህል ያስተማራቸውን አስራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ለአገልግሎት ያሰማራቸው ሥልጣንና



Scanned by CamScanner

መመሪያ ሰጥቷቸው ነው፤ (ማቴ. 28፡18 — 20፤ ማር. 16፡13

ደቀ መዛሙርትም ለአገልግሎት የለዩአቸውን ሰባት ሰዎች ያስማሩአቸው እጃቸውን ጭነው ከጸለዩላቸው በኋላ ነው (የሐዋ. ሥራ 6፡3 - 6)።

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያንም ከፍተኛ የሥነ መለኮት ትምህርት ተቋማት ትምህርታቸውን በሚገባ አጠናቅቀው የሚመረቁትን ዕጩ አገልጋዮች የምታስማራው በጉባዔ ፊት አቅርባ የእግዚአብሔርን ቃል መመሪያ በመስጠትና በመጸለይ ነው።

ዕጩ ተመራቂዎችም በሚሰማሩበት የአገልግሎት መስክ እግዚአብሔርን በመፍራትና ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች በመታዘዝ ፍሬ እንዲያፈሩ የቤተ ክርስቲያን ጸሎትና ተስፋ ነው። (1ጢሞ. 4፡1 - 16)

## 10.2 የምረቃ ሥርዓት ፕሮግራም ቅደም ተከተል

10.2.1 ተመራቂዎች የማዕረግ የምረቃ ልብሳቸውን ለብሰው ይዘጋጃሉ፤

10.2.2 የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ የከፍተኛ ትምህርት ጉባዔ አባላት፣ ጥሪ የተደረገላቸው የክብር እንግዶች፣ የተቋሙ ዲን፣ መምህራንና ዕጩ ተመራቂዎች በተቋሙ ዲሬክተር እየተመሩ በሰልፍ ወደ ምረቃው አዳራሽ ይገባሉ፤ የዕለቱ ፕሮግራም መሪም ጉባዔውን በማስዘመር እንግዶቹን ቆመው ይቀበላሉ፤

10.2.3 ሥነ ሥርዓቱ በጸሎት ይጀመራል፤

10.2.4 የጉባዔ መዝሙር ይዘመራል፤

10.2.5 መዘምራን ይዘምራሉ፤

10.2.6 ቃለ እግዚአብሔር ይቀርባል (ቢቻል መልእክቱ ከ20 ደቂቃ መብለጥ የለበትም)

10.2.7 የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተርና የአካዳሚክ ዲኑ በቅደም ተከተል ንግግር ያደርጋሉ፤



Scanned by CamScanner

10.2.8 ዲሬክተሩ፣ ዲኑና የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የወከለችው የክብር እንግዳ ለዕጩ ምሩቃን የትምህርት ማስረጃ ይሰጣሉ፤

10.2.9 የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዋና ጽ/ቤት የሚወክለው የክብር እንግዳ በትምህርት ቤቱ ዲን ጋባዥነት ተማሪዎችን ለመመረቅ ይዘጋጃል፤ ዕጩ ተመራቂዎችም እንደቆሙ በአንድነት የቆባቸውን መነሳነስ ወደ ግራ ያዞራሉ፤

10.2.10 በትምህርት ብልጫ ላገኙ ተማሪዎች ልዩ ሽልማት ይሰጣል፤

10.2.11 የምሩቃኑ ተወካይ ንግግር ያደርጋል፤

10.2.12 ምሩቃኑ የቀኝ እጃቸውን አንስተው የሚከተለውን ቃል ኪዳን ይገባሉ፡፡

## የምሩቃኑ ቃል ኪዳን

እኔ በእግዚአብሔርና በዚህ ጉባዔ ፊት የቆምኩ፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኜ አድርጌ ከተቀበልኩበት ጊዜ ጀምሮ፤ እግዚአብሔር ጸጋውን አብዝቶልኝ፤ ለቤቱ አገልግሎት እንደጠራኝና እንዳዘጋጀኝ አምናለሁ፡፡ በመሆኑም ለዚህ ታላቅ ጥሪና አገልግሎት ራሴን ሰጥቼ መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠኝ ኃይልና ብርታት እየታገዝኩ፡-

1. የእግዚአብሔርን ቃል በትጋት ለማስተማርና የደህንነትን የምሥራች ወንጌል ለማወጅ ቃል እገባለሁ፤
2. ቤተ ክርስቲያን በምታስማራኝና በምትልከኝ ቦታ ሁሉ በመታዘዝና በፍቅር ለማገልገል ቃል እገባለሁ፤
3. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሚፈጠሩ መለያየቶችና የስህተት ትምህርቶች ላለመተባበርና ምዕመናንን ወደ ትክክለኛው አቅጣጫ ለመምራት ቃል እገባለሁ፤
4. የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የእምነት አቋምና የመተዳደሪያ ደንብ በሚደነግገው መሰረት ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ለመታዘዝና ለማገልገል ቃል እገባለሁ፤*



Scanned by CamScanner

5. እውቀቴ፣ ችሎታዬንና ጊዜዬን ሳልቆጥብ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችና ምዕመኑ የሚጠብቅብኝን አገልግሎት ለመፈጸም ቃል እገባለሁ፤

6. እግዚአብሔር በሚሰጠኝ ረድዔት በመታገዝ በግልና በመንፈሳዊ ሕይወቴ መልካም ምሳሌ ሆኜ ለመኖር ቃል እገባለሁ፤

7. የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን በምትነድፈው የወንጌል ሥርጭት ራእይና ልዩ ልዩ ዕቅዶች በመሳተፍ በትጋት ለመተባበር ቃል እገባለሁ።

---

*ተመራቂዎች የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን አባል ካልሆኑ በራሳቸውን ቤተ ክርስቲያን ስም ይናገራሉ።

ቃል ኪዳኔን ለመፈጸም እግዚአብሔር ይርዳኝ።

አሜን!

10.2.13 ምሩቃኑ ተንበርክከው ከተጸለየላቸው በኋላ የምረቃው አስፈጻሚ ከመዝ. (121)፡3 — 8 ያለውን እንብቦ በቡራኬ ቃል ይፈጽማል፤

**እግዚአብሔር ይባርካችሁ፣ ይጠብቃችሁ፣**
**እግዚአብሔር ፊቱን ያብራላችሁ፣ ይራራላችሁም፤**
**እግዚአብሔር ፊቱን ወደናንተ ያንሳ፤**
**ሰላምንም ይስጣችሁ።**
**በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ አንድ አምላክ ስም።**
**አሜን።**

10.2.14 ምሩቃኑ በአንድነት ይዘምራሉ፤

10.2.15 መባ ይሰበሰባል፤

10.2.16 የመዝጊያ ጸሎት ተደርጎ የምረቃው ፕሮግራም ይጠናቀቃል።



Scanned by CamScanner

# 11. የመሰረት ድንጋይ የማኖር ሥርዓት

## መግቢያ፡-

በተለያዩ ጊዜያት የእግዚአብሔር ሰዎች ለእግዚአብሔር አገልግሎት የሚውሉ ሕንጻዎችን ለመሥራት የመሰረት ድንጋይ የጣሉበት ሁኔታ እንደነበር ከቃሉ እንረዳለን። በ2ኛ ዜና. 3፡1 — 3 ላይ "ሰለሞንም እግዚአብሔር ለአባቱ ለዳዊት በተገለጠበት በሞሪያ ተራራ ዳዊት ባዘጋጀው ስፍራ በኢያቡሳዊው በኦርና አውድማ በኢየሩሳሌም የእግዚአብሔርን ቤት መሥራት ጀመረ። በነገሥም በአራተኛው ዓመት በሁለተኛው ወር መሥራት ጀመረ። ሰሎሞንም የእግዚአብሔርን ቤት ይሠራ ዘንድ የጣለው መሰረት ይህ ነው፤ ርዝመቱም በዱሮው ስፍር ስድሳ ክንድ፥ ወርዱም ሃያ ክንድ ነበረ።" ይላል።

2ዜና. 8፡16 ላይም "የእግዚአብሔርም ቤት መሰረት ከተጣለ ጀምሮ እስከ ተጨረሰ ድረስ የሰሎሞን ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ነበረ። የእግዚአብሔርም ቤት ተፈጸመ።" ይላል። ሐጌ. 2፡18 "ከዛሬው ከዘጠነኛው ወር ከሃያ አራተኛው ቀን ጀምራችሁ የሚመጣውን ዘመን ልብ አድርጉ፤ የእግዚአብሔር መቅደስ መሰረት ከተተከለበት ቀን ጀምሮ ልብ አድርጉ።" ይላል።

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ዙሪያ ለሚሠሩ የጸሎት ቤቶች፣ የሥነ መለኮት ማሰልጠኛ ተቋማት፣ እና ልዩ ልዩ የአስተዳደርና የአገልግሎት መስጫ ቢሮዎችና ህንጻዎች ሲሠሩ አስቀድሞ የመሰረት ድንጋይ የማኖር ሥነ ሥርዓት ተከናውኖ እግዚአብሔር አምላካችን መመስገንና ለሥራው መጠናቀቅ ጸሎት መደረግ ይኖርበታል።

11.1 የመሰረት ድንጋይ የማኖር ሥርዓት ፕሮግራም ቅደም ተከተል ፕሮግራሙ በጸሎት ይጀመራል፤

11.2 የዕለቱ ፕሮግራም አስተባባሪ የምስጋና መዝሙር ያስዘምራል፤ ስለ ዕለቱ ፕሮግራምም አጭር መግለጫ ይሰጣል፤

11.3 መዘምራን የሚኖሩ ከሆነ ሁለት መዝሙሮችን ይዘምራሉ፤



Scanned by CamScanner

11.4 አጭር የመልእክት ጊዜ ይኖራል፤
11.5 የመሰረተ ድንጋይ የማኖሩ ሥርዓት በዕለቱ የክብር እንግዳ አማካኝነት ይፈጸማል፤
11.6 የክብር እንግዳው አጭር ንግግር ያደርጋል፤
11.7 ጉባኤው ወይንም መዘምራን ከዘመሩ በኋላ የመዝጊያ ጸሎት ተደርጎ የዕለቱ ፕሮግራም ይጠናቀቃል፡፡

## 12. የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ምረቃ ሥርዓት

### 12.1 መግቢያ፡-

በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት የሚከናወኑ ማናቸውም ነገሮች ለአምላካችን ክብር፤ ለሰው ልጆች ጥቅምና በረከት እንዲሆኑ ከእግዚአብሔር የተቀበልነውን በጎ ነገር ሁሉ መልሰን ለእግዚአብሔር በምስጋና ጸሎት ማስረከብ እንደሚገባን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ "አሁንም እንግዲህ አምላካችን ሆይ፣ እንገዛልሃለን፤ ለክቡር ስምህ ምስጋና እናቀርባለን፡፡ ሁሉ ከአንተ ዘንድ ነውና፣ ከእጅህም የተቀበልነውን ሰጥተንሃልና... አምላካችን ሆይ፣ ለቅዱስ ስምህ ቤት እንሠራ ዘንድ ይህ ያዘጋጀነው ባለጠግነት ሁሉ ከእጅህ የመጣ ነው፤ ሁሉም የአንተ ነው" (1ዜና. 29፡13 — 16)፡፡

ንጉሥ ሰለሞን ያሠራውን ቤተ መቅደስ ለማስመረቅ ከፍተኛ ጉባዔ በመጥራት ቤተ መቅደሱን ለእግዚአብሔር አስረከቧል፡፡ ልቡን በእግዚአብሔር ፊት አፍስሶ የምስጋና ጸሎት ጸልዮአል (1ነገ. 8፡1-66)፡፡ እግዚአብሔርም በዚህ ነገር ደስ ተሰኝቶ የምረቃውን ሥርዓት ስለተቀበለ ቤቱን በክብር እንደሞላው ቃሉ ይመሰክራል (2ዜና. 7፡1 — 3)፡፡

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የምታሠራቸው የጸሎት ቤት ሕንጻዎችም በሙሉ ለእግዚአብሔር ክብር እንዲውሉና የአምላካችንም መልካም ዓላማ እንዲፈጸም ሕንጻው አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት የምረቃ ሥነ - ሥርዓት አዘጋጅቶ አስቀድሞ ለእግዚአብሔር ማስረከብ እንደሚገባ ታምናለች፡፡

12..2 የቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ምረቃ ሥርዓት ፕሮግራም ቅደም ተከተል፡-

*ሀ/ ከሕንጻው ውጪ የሚደረግ ሥነ - ሥርዓት*

12.2.1 ጸሎት ተደርጎ የተዘጋጀው ጥብጣብ (ሪቫን) በዕለቱ የክብር እንግዳ አማካኝነት በመቀስ ይቆረጣል፤

12.2.2 ሁኔታዎች ተመቻችተው የሚዘጋጅ ከሆነ ለመታሰቢያ የተዘጋጀው ጽሑፍ ይገለጣል፤

*የመታሰቢያው ጽሑፍ ይዘት የሚከተለውን ይመስላል፤*

"ይህ የጸሎት ቤት ሕንጻ ለእግዚአብሔር ክብር፣ ለሰው ልጆች ጥቅምና አገልግሎት እንዲውል ________ ቀን ________ ዓ.ም ተመርቆ ተከፈተ።"

አስፈላጊ ከሆነ የእንግሊዝኛው አቻ ትርጉም አብሮ ሊጻፍ ይችላል።

"This Building was dedicated to the glory of God and to the peace and good will of men on ................"

12.2.3 የአዲሱን ሕንጻ የውጭና የውስጥ ይዘቱን ለመመልከት ጉብኝት ይደረጋል።

*ለ. ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚፈጸም ሥነ ሥርዓት*

12.2.4 ፕሮግራሙ በጸሎት ይጀመራል፤

12.2.5 የጉባዔ መዝሙር ይዘመራል፤

12.2.6 መዘምራን የመጀመሪያውን ክፍል ሁለት መዝሙር ያቀርባሉ፤

12.2.7 ለዕለቱ የተዘጋጀው ቃለ እግዚአብሔር ይቀርባል፤

12.2.8 በየቤተ ክርስቲያኒቱ ሥራ ለተባበሩት የተሳትፎ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤



Scanned by CamScanner

12.2.9 የማጠቃለያ ጸሎት ተደርጎ ሥነ - ሥርዓቱ ያበቃል፡፡

## 13. ልዩ ማሳሰቢያዎች

አንድ አገልጋይ በእግዚአብሔር አምላክና በሕዝቡ ፊት ሲቆም በአለባበሱ ንጹህ፣ ጭምትነትና ጨዋነት ያለው መሆን ይኖርበታል፡፡ የአምልኮ ፕሮግራም መሪዎች፣ የልዩ ልዩ ሥርዓት አስፈጻሚ አገልጋዮች፣ ቃለ እግዚአብሔር አቅራቢዎች፣ የፕሮግራም አስተናባሪዎች፣ መዘምራን ሁሉ ለአገልግሎት ሲቆሙ የልብሳቸውንና የመጫሚያቸውን ንጽህናና ጥራት ቢጠብቁ ለእግዚአብሔር ክብርና ለሌሎች መታነጽ ይሆናል፡፡

## 14. የገቢ አሰባሰብ

የቤተ ክርስቲያን ገቢዎች ደረሰኝ ተቆርጦላቸው በሥርዓት መሰብሰብ አለባቸው፡፡ ያለ ቤተ ክርስቲያኒቱ እውቅና ማንኛውም ግለሰብ ገቢ ማሰባሰብ የለበትም፡፡ በተጨማሪም ቤተ ክርስቲያናችን መጽሐፍ ቅዱሳዊውን መርህ ያልተከተለ የገቢ አሰባሰብ ሥርዓት ፈጽሞ አትቀበልም፡፡ ለምሳሌ፡- በጨረታ ዕቃዎችን የመሸጥ ሁኔታ ሥጋዊ ፉክክር ውስጥ የሚከትበት አካሄድ ስላለው መካሄድ የለበትም፡፡ በአሁኑ ዘመን አንዳንድ ግለሰቦች እንደሚያደርጉ የተጸለየበት ሻማ፣ የተጸለየበትና ዘይት የፈሰሰበት ጨርቅ፣ የተጸለየበት ውሃና ሌሎችም ቁሳቁሶች ሽያጭ ለገቢ ማሰባሰቢያ ሲውል ይታያል፡፡ እንዲህ ዓይነት ተግባራትን ቤተ ክርስቲያናችን ፈጽሞ አትቀበልም፡፡

## 15. የመዘምራን የደንብ ልብሶች ዓይነትና ቀለማት

### 15.1 መግቢያ፡-

በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ ያገለግሉ የነበሩ አገልጋዮች ለአምልኮና ለልዩ ልዩ ሥርዓቶች ወደ እግዚአብሔር ፊት ሲቀርቡ የተለየ ልብስና መጎናጸፊያ እንዲለብሱ እግዚአብሔር ራሱ ቀለማቱንና የስፌቱን ሞድ በግልጽ ያስታውቃቸው እንደነበር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በግልጽ ተጽፎ እናነባለን፡፡



Scanned by CamScanner

"አንተም ወንድምህን አሮንን ከእርሱም ጋር ልጆቹን፣ ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ ወደ አንተ አቅርብ፤ አሮንን የአሮንንም ልጆች... አቅርብ። የተቀደሰውን ልብስ ለክብርና ለጌጥ እንዲሆን ለወንድምህ ለአሮን ሥራለት። አንተም ካህን ሆኖ እንዲያገለግለኝ አሮን ቅዱስ ይሆን ዘንድ ልብስ እንዲሠሩለት የጥበብ መንፈስ ለሞላሁባቸው፣ በልባቸው ጥበበኞች ለሆኑት ሁሉ ተናገር። የሚሠሩአቸው ልብሶች እነዚህ ናቸው። ወርቅንም፣ ሰማያዊና ቀይም ግምጃ ጥሩ በፍታም ይውሰዱ" (ዘጸ. 28፡1 — 43)

በራእይ መጽሐፍ ውስጥም እንዲሁ "ከሕዝብና ከነገድ፣ ከወገንም፣ ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤" (ራእ. 7፡9) ይላል።

በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙ አገልጋዮች ሁሉ ራሳቸውን ቀድሰውና በጌጠኛና በክብር ልብስ አምረውና ተለይተው በዙፋኑ ፊት በጸጋ እንዲቀርቡ የእግዚአብሔር ሃሳብ ነው።

የይሁዳ ንጉሥ ኢዮሳፍጥም በጠላቶቹ በአሞንና በሞዓብ አጥፊዎች በተከበበ ጊዜ የወሰደው ርምጃ በሠራዊቱ ፊት የሚሄዱ ጌጠኛ ልብስ የለበሱ ዘማርያንን ማቆም ነበር። ከሕዝቡም ጋር ተማክሮ በሠራዊቱ ፊት የሚሄዱትን "ምህረቱ ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ፤ የሚሉትንም ጌጠኛ ልብስም ለብሰው የሚያመሰግኑትን ለእግዚአብሔርም የሚዘምሩትን መዘምራን አቆመ። ዝማሬውን፣ ምስጋናውንም በጀመሩ ጊዜ ይሁዳን ሊወጉ በመጡት... ላይ እግዚአብሔር ድብቅ ጦርን አመጣባቸው፤ እነርሱም ተመቱ" (2ዜና. 20፡20 — 22)።

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን መዘምራንም ከሚያገለግሉት ሕዝብ ተለይተው የሚታወቁባቸውን የክብርና የጌጥ ልብስ ለብሰው ማገልገላቸው ክብርና ሞገስ የሚጨምርላቸው ስለሆነ ተመሳሳይ የስፌት ሞድና ቀለማት ያላቸውን የደንብ ልብሶችን ለብሰው ማገልገላቸው መልካም እንደሆነ ታምኖበታል። በተጨማሪም ፋሽን



Scanned by CamScanner

ተከታይነትን ለመቀነስ፣ የአለባበስ ጨዋነትንና ጭምትነትን ለመጨመር፣ የአለባበስ ወጥነትን ለማምጣት ያለው ሚና ከፍተኛ ነው። ቀለማቱ በየኢትዮጲያ ቤተ ክርስቲያናቱ ፍላጎትና ምርጫ የሚወሰን ሆኖ የዘማርያንን የማዕረግ ልብስ በተመለከተ የስፌት ሞዱ ለመላው የቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ዘማርያን አንድና ወጥ ሆኖ እንዲዘጋጅ ተወስኗል።

## 15.2 የስፌት ሞድን በተመለከተ

### 15.2.1 የመዘምራን መለያ ልብስ፦

15.2.1.1 የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን የቡድን ዘማርያንም ሆኑ በግል ዝማሬ የሚያገለግሉ (ሶሎ ዘማርያን) አገልጋዮች የደንብ ልብስ የስፌት ሞድ አንድ ዓይነት መሆን ይገባዋል።

15.2.1.2 የደንብ ልብሱ ግማሽ አንገትን የሚሸፍን ክብ ኮሌታ፣ ስፋት ያለው ሙሉ እጅጌ፣ እስከ እግር የሚደርስ ሰፋ ተደርጎ የሚዘጋጅ ተጠላቂ ወይንም ከኋላ በኩል በከምስር የሚያያዝ ይሆናል፤

15.2.1.3 በደንብ ልብሱ ግራና ቀኝ በትከሻ የሚወርዱ ሁለት ጥብጣቦች (ስትራይፕ) ላይ "ወልድ ያለው ሕይወት አለው" የሚለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓርማ ይኖራል። በቀኝ ጥብጣብ (ስትራይፕ) ላይ ደግሞ ከቤተ ክርስቲያኒቱ ዓርማ ጋር በመጠኑ ተመጣጣኝ የሆነ የመስቀል ምልክት ይኖራል።

### 15.2.2 የጉባዔ አስተናጋጆች መለያ ልብስ፦

በአምልኮ፣ በኮንፍራንሶችና በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ፕሮግራሞች ላይ ተመድበው የሚያገለግሉ አስተናባሪዎች (አስተናጋጆች) ቀለሙ ሰማያዊ ሆኖ ቢጫ ዘርፍ ያለው በአንገት ላይ ተጠልቆ በቀኝ እጅ የሚወጣ ጥብጣብ ያደርጋሉ። በጥብጣቡ በግራ በኩል "ወልድ ያለው



Scanned by CamScanner

ሕይወት አለው" የሚለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓርማ ይኖራል።

### 15.2.3 የመጋቢያንና አገልግሎት አስፈጻሚዎች መለያ ልብስ፡-

የቤተ ክርስቲያን የመጋቢያንና የተለያዩ አገልግሎት አስፈጻሚዎች፡- ጥምቀት፣ የጌታ እራት፣ ሠርግና ለቅሶ ሥርዓቶችን ሲያስፈጽሙ መለያ ልብስ ሊኖራቸው ይገባል። ይህ መለያ ልብስ በቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያናት ወጥነት ያለው እንዲሆን ነጭ በሰማያዊ ተንጠልጣይ ሪቫን ይሆንና ሪቫኑ በቀኝ በኩል መስቀል በግራ በኩል "ወልድ ያለው ሕይወት አለው" የሚለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓርማ ይኖረዋል። የመለያ ልብሱ ጋወን ባለ ሰማያዊ ጥብጣብ መቀነት እንዲኖረው ተደርጎ ይሠራል።

### 15.2.4 የጥበቃ አገልጋዮች መለያ ልብስ

ወቅቱ አስቸጋሪ እየሆነ በመምጣቱ ወደ ቤተ ጸሎት የሚገቡ ሰዎችን ለይቶ ለማወቅ ቢቻልም እንደ አስፈላጊነቱ ፍተሻ ለማድረግ አስገዳጅ ሁኔታዎች ቢፈጠሩ ይህንን ለመተግበር እንዲችል የጥበቃ አገልጋይ መለዮ ለባሽ ቢሆን ይመረጣል።

## 16. የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓርማ

በወንጌል አማኞች አንድነት ማኅበር የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዓርማን በተመለከተ በመተዳደሪያ ደንቡ ክፍል አንድ ንዑስ ቁጥር 3 ላይ ቅርጽና ይዘቱ ምን መሆን እንዳለበት እንደሚከተለው ተገልጿል።

"የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓርማ መጽሐፍ ቅዱስ ተገልጦ በውስጡ ወልድ ያለው ሕይወት አለው የሚል ነው።"

ቢሆንም ግን በአንዳንድ አጋጣሚዎች ዓርማው በማኅተሞች፣ በጨርቆች፣ በሰሌዳዎችና በልዩ ልዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ ሲቀረጽ ትክክለኛውን ቅርጽ መያዝ ስለሚገባው ቤተ ክርስቲያናት የዓርማውን ትክክለኛ ቅጂ ሊጠቀሙ ይገባል። የቤተ ክርስቲያኒቱ ዓርማ ትክክለኛ ቅርጽ በዚህ መጽሐፍ የመጨረሻ ክፍል ላይ ተመልክቷል።



Scanned by CamScanner

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ዓርማ



Scanned by CamScanner

# ክፍል ሁለት

# የምስክር ወረቀቶች



Scanned by CamScanner

# የልደት የምስክር ወረቀት ናሙና

ፎቶ

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
የ ________ ቃለ ሕይወት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን
________ KALE HEYWET CHURCH
"እነሆ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው"
መዝ. 126 (127)

ቁጥር ________
Ref. No

## የልደት የምስክር ወረቀት
## BIRTH CERTIFICATE

የሕጻኑ (ኗ) ስም ________ ፆታ ________
Name of the Child ________ Sex ________
የተወለደበት (ችበት) ቀን ________ ሰዓት ________
Date of Birth ________ Time ________
የተወለደበት (ችበት) ስፍራ ________
Place of Birth ________
የአባት ስም ________ ዜግነት ________
Fathers Name ________ Nationality ________
የእናት ስም ________ ዜግነት ________
Mother's Name ________ Nationality ________
የምስክር ወረቀቱ የተሰጠበት ቀን ________
Date of Issue ________

________________________

የሰብሳቢው (የተጠሪው) ስምና ፊርማ
The Chairman's (Authorized) Signature



Scanned by CamScanner

# የአባልነት መታወቂያ ናሙና

የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
KALE HEYWET CHURCH

ማሳሰቢያ
ይህን መታወቂያ ካርድ የያዙት የቤተ ክርስቲያናችን አባል በመሆናቸው ትብብር እንዲደረግላቸው እንጠይቃለን።

የአባልነት
መታወቂያ ካርድ
Identify Card

ሙሉ ስም ____________
Name ____________
ዜግነት ____________
Nationality ____________
አባል የሆኑበት ዓመት ____________
Date of Membership ____________
የአገልግሎት ድርሻ ____________
Church Service ____________
ወረዳ ______ ቀበሌ ______ የቤት.ቁ ______
Wor. Keb. Home No.
ስልክ ቁ. ______ የቤት ቁ. ______
Tel No. Res
የቢሮ ______
Off.

የ__________ ቃለ ሕይወት ቤ/ክ
መታወቂያ ካርድ ቁ.__________
ከ ______ ዓ.ም እስከ ____ ዓ.ም
ብቻ ነው።

ፎቶ

የቤተ ክርስቲያኒቱ ስልክ ______

የተሰጠበት ቀን ____________
Date of Issue ____________

የሰብሳቢው (የተጠሪው) ፊርማ ____________
Authorized Signature ____________



Scanned by CamScanner

## የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን ብሔራዊ የጥምቀት የምስክር ወረቀት ናሙና

በኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
የ_______________ቃለ ሕይወት ቤተ ክርስቲያን
_______________KALE HEYWET CHURCH

ፎቶ

**የጥምቀት የምስክር ወረቀት**
**BAPTISM CERTIFICATE**

ሙሉ ስም______________________________
Full Name__________________________
የትውልድዘመን__________________
Date of Birth__________________
ዜግነት_______________________
Nationality_____________________

በ _________ቀን______ዓ.ም የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት በሚደነግገው መሰረት ተገቢውን የደኅንነት እና የጥምቀት ትምህርት ተከታትለው በማጠናቀቃቸው ይህ የምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸዋል።

_________________________ _________________________

| | |
|---|---|
| የሰብሳቢ (ተጠሪ) ስምና ፊርማ | ጋብቻውን ያስፈጸመው ስምና ፊርማ |
| The Chairman's (Authorized) Signature | Baptised by |



Scanned by CamScanner

Scanned by CamScanner